# የራስን ሥነ-መለኮት መገንባት

## ትምህርት 4

## ሥልጣን በሥነ-መለኮት

Manuscript

thirdmill
Biblical Education. For the World. For Free.

© 2019 by Third Millennium Ministries

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከአሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ውጭ ማጠቀሻነት፣ ለግምገማ ፣ ለአስተያየት ወይም ለትምህርት ዓላማዎች በአጭሩ መጠቀም ካልሆነ በስተቀር የዚህ ጽሑፍ ክፍል በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ ለትርፍ ሊባዛ አይችልም። የአሳታሚው አድራሻ Third Millennium Ministries, Inc., 316 Live Oaks Blvd., Casselberry, Florida 32707.

በሌላ መንገድ ካልተጠቆመ በስተቀር ፣ ሁሉም የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች በ1954 ዓ.ም ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ናቸው።

## ስለሴርድሚል

እ.ኤ.አ. በ 1997 የተቋቋመው ፣ ሴርድሚል ለትርፍ ያልተቋቋመ የወንጌላዊ ክርስቲያናዊ አገልግሎት ሲሆን

**መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት፣ ለዓለም፣ በነጻ ይሰጣል፡፡**

ግባችን በዓለም ዙሪያ በመቶ ሺዎች ለሚቆጠሩ ፓስተሮች እና ለአገልግሎት በቂ ሥልጠና ለሌላቸው የክርስቲያን መሪዎች ነፃ የክርስትና ትምህርት መስጠት ነው። በእንግሊዝኛ ፣ በአረብኛ ፣ በማንዳሪን ፣ በሩሲያኛ እና በስፓኒሽ ተወዳዳሪ የሌለውን የመልቲሚዲያ ሴሚናሪ ሥርዓተ ትምህርት በማዘጋጀት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በማሰራጨት ይህንን ግብ እያሟላን እንገኛለን። በአጋር መሥሪያ ቤቶቻችን አማካኝነት ሥርዓተ ትምህርታችን ከአሥር በላይ በሚሆኑ ሌሎች ቋንቋዎችም እየተተረጎመ ነው። ሥርዓተ ትምህርቱ በጥሩ ግራፊክ የተሠሩ ቪዲዮዎችን፣ የታተሙ ትምህርቶችን እና የበይነመረብ ግብዓቶችን ያካትታል። በትምህርት ቤቶች ፣ በቡድኖች እና በግለሰቦች ፣ በበይነመረብም ሆነ በትምህርት ማህበረሰቦች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውል የተቀየሰ ነው።

ባለፉት ዓመታት፣ እጅግ በጣም ጥሩ ይዘትን እና ጥራትን የተሸለሙ የመልቲሚዲያ ትምህርቶችን ለማምረት ከፍተኛ ወጪ ቆጣቢ ዘዴን አዘጋጅተናል። ጸሐፊዎቻችን እና አርታኢዎቻችን በስነ-መለኮት የሰለጠኑ አስተማሪዎች ፣ ተርጓሚዎቻችን የሥነ-መለኮታዊ አስተውሎት ያላቸውና የሚተረጉሙበት ቋንቋዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የሆናቸው ናቸው ፣ እንሁም ትምህርቶቻችን ከዓለም ዙሪያ የመጡ በመቶዎች የሚቆጠሩ የተከበሩ የሴሚናሪ ፕሮፌሰሮች እና ፓስተሮች አሳቦችን ይዘዋል። በተጨማሪም ፣ የእኛ ግራፊክ ዲዛይነሮች ፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች እና አዘጋጆች ዘመናዊ መሣሪያዎችን እና ቴክኒኮችን በመጠቀም ከፍተኛውን የዝግጅት ደረጃዎችን የሚያሟሉ ናቸው፡፡

የስርጭት ግቦቻችንን ለማሳካት ፣ ሴርድሚል ከቤተክርስቲያናት ፣ ከሴሚናሪዎች ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ፣ ከሚሲዮናውያን ፣ ከክርስቲያን ማሰራጫዎች እና ከሳተላይት ቴሌቪዥን አቅራቢዎች እና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ስትራቴጂካዊ አጋርነት ፈጥሯል። እነዚህ ግንኙነቶች ቀደም ሲል ስፍር ቁጥር የሌላቸው የቪዲዮ ትምህርቶችን ለአገሬው ተወላጅ መሪዎች ፣ ለፓስተሮች እና ለሴሚናሪ ተማሪዎች ማሰራጨት አስችሏል። የድረ-ገጾቻችን እንዲሁ እንደ ስርጭት መንገዶች ሆነው ያገለግላሉ እንዲሁም የመማሪያ ማህበረሰብ እንዴት እንደሚጀምሩ ግብዓቶቸንና ትምህርቶቻችንን ለማግኘት ተጨማሪ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

ሴርድሚል በ IRS እንደ 501 (ሐ) (3) ኮርፖሬሽን እውቅና ተሰጥቶታል። እኛ ገቢ የምናገኘው ከአብያተ-ክርስቲያናት ፣ ፋውንዴሽንስ፣ ንግድ ተቋማት እና ግለሰቦች በሚሰጡት አርዳታ ነው፡፡ ሰዎች ለእኛ ሲለግሱ ከሚከፍሉት ግብር ይቀነስላቸዋል፡፡ ስለአገልግሎታችን ተጨማሪ መረጃ ፣ እና እርስዎ እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ለማወቅ ፣ እባክዎ www.thirdmill.org ን ይጎብኙ።

# የራስን ሥነ-መለኮት መገንባትተ

## ትምህርት አራት

## ሥልጣን በሥነ-መለኮት

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| መግቢያ | 3 |
| የመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊካዊነት | 3 |
| የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን | 3 |
| በመንፈስ ቅዱስ መነዳት | 4 |
| ትርጉም | 4 |
| ደብዛዛነቱ/ድብቅነቱ | 5 |
| የቤተክርስቲያን ሥልጣን | 6 |
| የቀደሙ ባለሥልጣናት | 6 |
| የዘመኑ ባለሥልጣናት | 7 |
| የመጀመሪያዎቹ ፕሮቴስታንቶች | 8 |
| የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን | 8 |
| በመንፈስ ቅዱስ መነዳት | 9 |
| ትርጉም | 10 |
| ግልጽነት | 12 |
| የቤተክርስቲያን ሥልጣን | 13 |
| የቀደሙ ባለሥልጣናት | 14 |
| የዘመኑ ባለሥልጣናት | 15 |
| ወቅታዊ ፕሮቴስታንትዝም | 16 |
| የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን | 16 |
| ትርጉም | 19 |
| ግልጽነት | 20 |
| የቤተክርስቲያን ሥልጣን | 23 |
| የዘመኑ ባለሥልጣናት | 25 |
| ማጠቃለያ | 27 |
| አስተዋፅዖ አድራጊዎች | 28 |




ቪዲዮዎችን፣ የትምህርት መመሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን ለማግኘት Thirdmill at thirdmill.org. ይመልከቱ.

## መግቢያ

ባለሥልጣናትን በመከተል ምን ያህል ሕይወታችንን እንደምናሳልፍ አስተውለሃል? በዘመናዊው ዓለም ይህንን ለመናገር እንግዳ እንደሚመስል አውቃለሁ ፣ ግን እውነት ነው። መኪና ሲበላሽ ስለ መኪናዎች ብዙ የሚያውቅ ሰው እንፈልጋለን። ስንታመም በሕክምና ውስጥ የታወቀ ሰው እንፈልጋለን። እነዚህ ባለሙያዎች በሚሉት ሁሉ ነገር ላንስማማ እንችላለን፣ ግን እነዚህን እና ሌሎች ውስብስብ ጉዳዮችን በራሳችን ለማስተናገድ አንሞክርም። በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ማለት ይቻላል ፣ ጥበበኞች ከሆንን፣ ትክክለኛ በመስካቸው ተሰሚነት ያላቸውን ሰዎች እንፈልጋለን፣ የሚሉትንም በጥሞና እናዳምጣለን።

በክርስትና ሥነ -መለኮትም ውስጥ እንደዚህ ያለ ነገር እውነት መሆን አለበት። ብዙውን ጊዜ፣ ጥሩ ስሜት ያላቸው ክርስቲያኖች ሥነ-መለኮትን መማር እና መኖር የግል ጉዳይ ስለሆነ በመስኩ ትልልቅ የሚባሉ ሰዎችን እርዳታ መፈለግ አያስፈልግ ብለው ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ አለን እናም ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት አለን። ይህ በቂ አይደለም? ነገር ግን በዚህ ትምህርት እንደምንመለከተው ፣ እግዚአብሔር ሥነ-መለኮታችንን ስንገነባ እኛን ለመርዳት በርካታ ሥልጣን ያላቸውን አካላት ሾሟል።

ሥነ-መለኮትን መገንባት በሚለው ተከታታይ ትምህርቶች ውስጥ ይህ ሥልጣን በሥነ-መለኮት ውስጥ የሚለው አራተኛ ትምህርት ነው። የእኛን ሥነ-መለኮት ስንገነባ ተገቢውን አካላት በማግኘት እና በመከተል ውስጥ የተካተቱ አንዳንድ መሠረታዊ ጉዳዮችን እንመረምራለን።

*ክርስቲያኖች በሦስት የተለያዩ የቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ሥልጣን በሥነ -መለኮት ውስጥ ባስተናገዱባቸው መንገዶች ላይ እናተኩራለን። በመጀመሪያ በመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክ እምነት ውስጥ ስለ ሥነ-መለኮታዊ ሥልጣን ያለውን አመለካከት ጠቅለል አድርገን እናቀርባለን። ሁለተኛ በመጀመሪያ የፕሮቴስታንት እምነት ውስጥ ለሥነ-መለኮታዊ ሥልጣን የነበረውን አቀራረብ እንመረምራለን። ሦስተኛ በዘመናዊ ፕሮቴስታንት ውስጥ እነዚህን ጉዳዮች እንዴት መያዝ እንዳለብን እንመረምራለን። ሥልጣን በክርስትና ሥነ-መለኮት ውስጥ በሚለው ላይ የመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክን አመለካከት በመመልከት እንጀምር።*

## *የመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊካዊነት*

ይህ ተከታታይ ትምህርት በወንጌላውያን ፕሮቴስታንት ሥነ-መለኮት ላይ ያተኮረ መሆኑን ቀደም ባለው ትምህርት ተናግረናል። የቤተክርስቲያን የፕሮቴስታንት ቅርንጫፎች በሥነ-መለኮት ውስጥ ስልጣንን እንዴት እንደሚመለከቱ ለመረዳት፣ እነዚህ ወጎች ከፕሮቴስታንት ተሃድሶ እንዴት እንደመጡ ማየት አስፈላጊ ነው። አሁን የፕሮቴስታንት ተሐድሶ በብዙ ምክንያቶች ተከናወነ፣ ነገር ግን ከዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች አንዱ በመካከለኛው ዘመን በሮማ ካቶሊክ እምነት ውስጥ በነበረው የሃይማኖት ሥልጣን ላይ አለመግባባት ነበር። እነዚህ አመለካከቶች እና ልምዶች በሥነ-መለኮት ላይ ስለሚኖረው ሥልጣን ለፕሮቴስታንት አመለካከቶች ወሳኝ ዳራ ፈጥረዋል።

*የመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክን ስንመረምር ፣ ሁለት ርዕሶችን እንዳስሳለን- በመጀመሪያ ፣ በመካከለኛው ዘመን ቤተክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን እና ሁለተኛው፣ በቤተክርስቲያን ሥልጣን ላይ የነበረው አመለካከት ነው። በመካከለኛው ዘመን በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን በመጀመሪያ እንመልከት።*

### *የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን*

*ተሐድሶው ከመደረጉ በፊትም እንኳ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ግለሰቦችና ትዕዛዛት በተለያዩ መንገዶች ቅዱሳት መጻሕፍትን ያስተናግዱ ነበር። ግን እጅግ በጣም ብዙ የመካከለኛው ዘመን የነገረ -መለኮት ምሁራን በቅዱሳት መጻሕፍት*

ሥልጣን ቢያንስ በንድፈ ሀሳብ ያምናሉ ብሎ መናገር ተገቢ ነው። በተግባር ግን ፣ የመካከለኛው ዘመን ቤተክርስቲያን ለመጽሐፍ ቅዱስ የነበራት አቋም ለቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን በቁርጠኝነተ ለመገዛትና ተግባራዊ ለማድረግ ፈጽሞ የማይቻል ነበር።

የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን በተመለከተ የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ችግር ስንመረምር ፣ በሦስት ጉዳዮች ላይ እንዳስሳለን። በመጀመሪያ፣ በመካከለኛው ዘመን ወቅት ስለመጽሐፍ ቅዱሳዊ አነሳሽነት ያለውን ጽንፍ እይታ እንመለከታለን። ሁለተኛ ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ላይ ከልክ ያለፈ እይታዎችን እንመለከታለን። ሦስተኛ ፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ደብዛዛነት የተጋነኑ የይገባኛል ጥያቄዎችን እንመረምራለን። እስቲ በመጀመሪያ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አነሳሽነት በመካከለኛው ዘመን የነበረውን አመለካከት እናስብ።

## በመንፈስ ቅዱስ መነዳት

በአጠቃላይ የመካከለኛው ዘመን የካቶሊክ የሃይማኖት ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ በአምላክ መንፈስ መሪነት የተጻፈ መሆኑን እና ሰዎች እንደ መሣሪያዎች ሆነው የመጣ መሆኑን አረጋግጠዋል። እንደ አለመታደል ሆኖ ግን በዚህ የቤተክርስቲያን ታሪክ ዘመን ብዙ የሥነ-መለኮት ምሁራን በመንፈስ መነዳት/መምራትን የተረዱበት መንገድ ጽንፍ የያዘ ነበር፡፡ እነርሱ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሰብዓዊ እና ታሪካዊ አመጣጥ ችላ በማለት የቅዱስ መጽሐፍን መለኮታዊ አመጣጥ ላይ አፅንዖት ሰጥተዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ አመጣጥ ላይ የመካከለኛው ዘመን ትኩረት የመጣው በብዙ ምክንያቶች ነው። አንደኛው ፣ የመካከለኛው ዘመን የነገረ-መለኮት ሊቃውንት በብዙ መንገድ የክርስትና ሥነ-መለኮትን ምድቦች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እንደ ኒዮ-ፕላቶኒዝም እና አርስቶቴሊያኒዝም ባሉ የግሪክ ፍልስፍናዎች ላይ በጣም ጥገኛ ስለነበሩ ነው። እነዚህ ፍልስፍናዎች ከጊዜያዊ እና ከታሪካዊ እውነታዎች ይልቅ የዘለአለማዊ እውነታዎችን ዋጋ ሰጥተዋል። ስለዚህ ፣ የክርስትና ሥነ-መለኮት ምሁራን የቅዱሳት መጻሕፍት ታሪካዊ እና የሰዎች ሚና ከሰማያዊው አመጣጥ አንጻር አላስፈላጊ እንደሆነ አሰቡ፡፡

ከዚህ ባሻገር የመካከለኛው ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ጥንታዊ ታሪክ በጣም ስለማያውቁ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ ዳራዎችን በስነ-መለኮታቸው ውስጥ ብዙ በተግባር መጠቀም አልቻሉም። ከዚያ ይልቅ ለሚያውቁት ነገር አፅንዖት ሰጥተዋል - ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ ዘላለማዊው የሰማይ አምላክ የገለጠላቸውን ጊዜ የማይሽራቸው እውነቶች ይዟል የሚል ሰሆን ሌሎች ሀሳቦችን በአብዛኛው ዝቅ አድርገውታል።

የመካከለኛው ዘመን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ምሪት መጻፉን የነበራቸው አመለካከት የቅዱሳት መጻሕፍትን ሙሉ ሥልጣን ለመጠቀም ተስፋ ያስቆረጠ ብቸኛው ጉዳይ አልነበረም። የመካከለኛው ዘመን ቤተክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ አመጣጥ ላይ ያሳደረችው ውጥረት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም አሳዛኝ እምነትንም አስከትሏል።

## ትርጉም

ቅዱሳት መጻሕፍት ከሰማይ የመጣ ነው የሚል እምነት ስለነበር ሌሎች መጻሕፍት እንደሚተረጉሙት መጽሐፍ ቅዱስ መተርጎም የለበትም የሚል ግምት ነበር፡፡ እግዚአብሔር በመንፈሱ ስላመጣው፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በትርጉሞች የተሞሉ ናቸው ይባል ነበር፡፡ ብዙ የመካከለኛው ዘመን የነገረ -መለኮት ምሁራን አወጉስቲንን በመከተል መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ምሪነት ስለመጻፉ አንዱ የቅዱሳት መጻሕፍት ጽሑፎች ብዙ ትርጉሞች እንዳሏቸው አምነዋል፡፡

አውግስቲን በክርስቲያን ዶክትሪን መጽሐፍ መጽሐፍ 3 ምዕራፍ 27 ላይ ያስቀመጠውን መንገድ ያዳምጡ

> *ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ትርጓሜዎች በተመሳሳይ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት ላይ ሲደረጉ ፣ ምንም እንኳን ጸሐፊው የፈለገው ትርጉም ባይገለጽም ምንም አደጋ የለም… እግዚአብሔር በቅዱሳን መጻሕፍት ተመሳሳይ ቃላት የተለያዩ ትርጉሞችን እንዲሰጡ በማድረግ ብዙ ነጻነትና ዕድልን ከመስጠት በላይ ምን ይሰጣል?*

በብዙ መንገዶች ፣ አውጉስቲን ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ያለውን ከፍተኛ እይታ ማድነቅ እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ ተራ መጽሐፍ አይደለም ፣ ልዩ ባሕርያቱ ወደ መለኮታዊ አነሳሱ ያመለክታሉ። እንዲሁም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጽታዎች ሊብራሩ የሚችሉት ከጽሑፉ በላይ ከተፈጥሮ በላይ በሆነው የእግዚአብሔር ቁጥጥር ብቻ እንደሆነ መስማማት እንችላለን። ነገር ግን የአውጉስቲን አመለካከት ከዚህ እጅግ የላቀ ነበር። መለኮታዊ አነሳሽነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ምንባቦች በበርካታ ትርጉሞች እንዲኖራቸው እንዳደረገ ያምናል። ስለዚህ አውግስቲን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰብዓዊ ደራሲዎች ለማስተላለፍ ካሰቡት ነገር ጋር ራሳችንን ከማስጨነቅ ይልቅ ትኩረታችንን እግዚአብሔር ባሰባቸው ብዙ ትርጉሞች ላይ ማተኮር እንዳለብን

ያምናል። ለዓላማችን ፣ የአውግስቲን እይታ እና ተዛማጅ እይታዎችን ፣ "ክላሲካል ብዝሃነት" ብለን እንጠራዋለን - የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ከእግዚአብሔር የመጡ በመሆናቸው ብዙ ትርጉም ወይም እሴት አላቸው የሚል እምነት ነው።

ምናልባት በሰፊው የሚታወቀው የጥንታዊ ብዝሃነት መግለጫ "ኳድሪጋ" በመባል በሚታወቀው በጆን ካሲያን ዘንድ የተስፋፋው የትርጓሜ አቀራረብ ሊሆን ይችላል። በዚህ አቀራረብ መሠረት እያንዳንዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፍ አራት የተለያዩ ትርጉሞች እንዳሉት መታየት አለበት። በመጀመሪያ ቀጥተኛ ትርጉሙ የአንድ ጽሑፍ ግልፅ ወይም ተራ ትርጉም ነበር። ሁለተኛ ምሳሌያዊ ትርጉሙ ጽሑፎችን ለትምህርታዊ እውነት መጠቀም ነው:: ሦስተኛ ትሮፖሎጂያዊ ወይም ሥነ ምግባራዊ ሲሆን ለክርስቲያናዊ ሥነ ምግባራዊ መመሪያዎችን ማውጣት ነው:: አራተኛ አናጎጂካዊ ትርጉም ሲሆን በመለኮታዊው ተስፋዎች ወይም በመጨረሻዎቹ ቀናት የሚሆኑ ጉዳዮችን ያመለክታል።

የኳድሪጋ ዝርዝሮች እና ሌሎች የክላሲካል ብዝሃነት መግለጫዎች ለዓላማችን አስፈላጊ አይደሉም - ብዙ ጸሐፊዎች በሌላ ቦታ አብራርተዋል። እኛ በተሃድሶው ጊዜ ፣ አብዛኛዎቹ የካቶሊክ ሃይማኖታዊ ሊቃውንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ትርጉሞች ከተለመደው ትርጉም በላይ እንደሄዱ በቀላሉ ማወቅ አለብን። በከፍተኛ ሁኔታ ፣ እነዚህ ተጨማሪ ትርጉሞች የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲዎች ለማስተላለፍ ባሰቡት ትርጉም ላይ የተመሠረተ እንዳልሆነ ያምናሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ የአንድ ምንባብ ቃል በቃል ወይም በግልጽ ብዙውን ጊዜ ለጠንካራ ሥነ -መለኮታዊ ማሰላሰል የመጀመሪያ ደረጃ ተደርጎ ይቆጠር ነበር። ይልቁንም ፣ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ጥልቅ የሆነውን ፣ የተደበቁትን የትርጉም ንብርብሮች ዋጋ እንዲሰጡ ተበረታተዋል፣ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን የአዕምሮ ጥልቀት ለቤተክርስቲያን ገልጠዋል ተብሎ ስለሚታመን።

> *ስለዚህ ፣ ይህ የቅዱሳት መጻሕፍት የተደበቀ ትርጉም መኖሩ በእውነቱ አስደሳች ነው ምክንያቱም እኛ ሁለቱንም በጥልቀት ከተመለከትን ችግሮች አሉ… ከእነርሱም አንዱ ይህንን ጥልቅ ትርጉም በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ለመጫን ወደመሞከር ይወስደናል:: ያ መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ የሚገልጠው መልዕክት ላይ ትኩረት እንዳናደርግ ያደርገናል:: «ግን ሌላ ምን ማለት ነው?" … ጥልቅ ትርጉሙም አንዳንዶቻችንን በቤተክርስቲያን ውስጥ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል አንደምታ አለው።… ይህንን ቀሳውስቱ በመሠረታዊነት በጣም አስፈላጊ የሰዎች ቡድን በነበሩበት በመካከለኛው ዘመን ቤተክርስቲያን እናየዋለን። ተራ ሰዎች ላዩን ትርጉምን ብቻ ማየት ስለሚችሉ ቅዱሳት መጻሕፍት በተራ ሰዎች እጅ እንዳይገባ መጠበቅ ይጠበቅ ነበረ:: ተራ ሰዎች ጥልቅ ትርጉሙን ለማየት የሚያስችል ችሎታ፣ ሥልጠና ክህሎት አልነበራቸውም። እናም ወደ ኋላ ተመልሰን የመካከለኛው ዘመን ሥነ -መለኮትን ከተመለከትን ፣ ወደ እነዚህ ጥልቅ ምሳሌያዊ ንባቦች ውስጥ ብዙ ርቀት ሄደው ነበር ፣ እና በእያንዳንዱ ጽሑፍ ውስጥ በርካታ ትርጉሞች ነበሩ ፣ ግን ብዙ ሰዎች ወደ ጥልቅዎቹ ትርጉሞች መድረስ አልቻሉም ተብሎ ይታመን ነበር።*
>
> — ዶ/ር ቲም ሳንስበሪ

የመካከለኛው ዘመን ስለቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጻፍና ትርጉም ስንመለከት በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ላይ ተግዳሮት ሆኖ ነበር:: እነዚህ አቀራረቦች እንዲሁ በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ባህርይ - ድብቅነቱ - ላይ ከመጠን በላይ ትኩረት እንዲሰጥ አድርጓል:: መጽሐፍ ቅዱስ ለየት ያለ ከተፈጥሮ በላይ ግንዛቤ ከተሰጣቸው በስተቀር ለሌሎች ሰዎች ግልፅ ያልሆነ መጽሐፍ ተደርጎ ይወሰድ ነበረ::

## ደብዛዛነቱ/ድብቅነቱ

የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘት ከተሃድሶው በፊት ለአማካይ ክርስቲያን ግልጽ ያልሆነ መስሎ መታየቱ ሊያስደንቀን አይገባም። ማንበብና መጻፍ ዝቅተኛ ነበር። መጽሐፍ ቅዱሶች በጣም ጥቂቶች ስለነበሩ ማንም መጽሐፍትን ማግኘት አይችልም ነበር። ከዚህም በላይ ላቲን የቅዱሳት መጻሕፍት እና ሥነ -መለኮት ተቀዳሚ ቋንቋ ነበር ፣ እና በአብዛኛው ፣ በጣም የተማረው ብቻ ነበር ላቲንን በደንብ ተረድቶ ብዙ መጠቀም የሚችለው። ስለዚህ እኛ ዛሬ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደምናጠና የሚያጠኑ ጥቂት ሰዎች ነበሩ:: ተራው ክርስቲያን ጉልህ በሆነ መንገድ በቀጥታ በእርሱ ላይ መታመን እንዲችል መጽሐፍ ቅዱስን አያገኝም እንዲሁም ግልጽ ያልሆነ ተደርጎ ይቆጠር ነበር።

ቅዱሳት መጻሕፍት ለአማካይ ክርስቲያን ዝግ ነበር:: በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ችሎታ እና ዕድል ላላቸው ሰዎች እንኳን ግልፅ እንዳልሆኑ ይታሰብ ነበር። በመካከለኛው ዘመን የነገረ-መለኮት ሊቃውንት እንደሚሉት፣ እግዚአብሔር ከቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ ከብዙዎቹ እይታ የተሰወሩ በርካታ የትርጉም ንብርቦችን አስቀምጧል።.

አንድ ሰው የተዘጋ ሀብት ሣጥን ሲያሳያችሁ እና በሳጥኑ ውስጥ ምን ዓይነት ውድ ሀብቶች እንዳሉበት እንድትናገሩ ብጠይቃችሁ ምን እንደምትመልሱ አስቡ፡፡ በእርግጥ ፣ ሀብቶቹ ተደብቀዋል ምክንያቱም በሳጥኑ ውስጥ ያለውን ማወቅ አይቻልም። በመካከለኛው ዘመን ቤተክርስቲያን ውስጥ ለመጽሐፍ ቅዱስ ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር።

በተሐድሶው ዘመን ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ደብዛዛነት ማመን መጽሐፍ ቅዱስ በሥነ -መለኮት እድገት ላይ ብዙ ተግባራዊ ወይም እውነተኛ ሥልጣን እንዲኖረው ፈጽሞ የማይቻል ነበር። በንድፈ ሀሳብ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ አነሳሽነት የተጻፈ ለክርስቲያናዊ ሥነ -መለኮት ጠቃሚ የሆነ ሀብት ሣጣን ውስጥ ተዘግቶበታል፤ ግን ለሁሉም ተግባራዊ ዓላማዎች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ተዘግቷል። በጣም ድብቅ እንደሆነ ከመታመኑ የተነሣ የነገረ-መለኮት ምሁራንን በተግባራቸው መምራት አልቻለም።

> *በመካከለኛው ዘመን ቤተክርስቲያን ውስጥ አብዛኛዎቹ አማኞች በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ሙሉ ዓላማ በአራት እጥፍ አቀራረብ የሚታወቅ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ እነርሱም ሥነ ምግባራዊው ቃል በቃል፣ ሥነ -ጽሑፍ እና ምሳሌያዊ። ስለዚህ የአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ተሃድሶ አራማጆች - በብዙዎቻችን "ፕሮቴስታንቶች" በመባል ይታወቃሉ - ይህንን ንድፈ ሀሳብ ይቃወሙ ነበር፡፡ በእነርሱ እይታ ይህ መጽሐፍ ቅዱስን መበከል እንደሆነ ያምኑ ነበር፡፡ ይህ ንድፈ-አሳብ የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያ ዓላማና ሥልጣን ያደበዘዘ ነበር፡፡ ይህም የሆነ ሆን ተብሎ የቤተክርስቲያን ሥልጣን ከመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን እንዲበልጥ ለማድረግ ነበር፡፡*
>
> — ዶ/ር ጀምስ ዲ ስሚዝ III

የመካከለኛው ዘመን የሮማን ካቶሊክ የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣንን በአዕምሯችን ይዘን ወደ ሁለተኛው አስተሳሰባችን ለመሸጋገር ዝግጁ ነን - በመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ሥነ-መለኮት ሥልጣንን እንመልከት።

## የቤተክርስቲያን ሥልጣን

የመካከለኛው ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ መሪነት መጻፍ፣ ትርጉምና መደበቅ አስተምህሮ ከባድ የሆኑ ጥያቄዎች እንዲነሱ ምክንያት ሆነ፡፡ አማኞች ቅዱሳት መጻሕፍትን ለራሳቸው ማስተናገድ በማይችሉበት ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት በአማኞች ላይ ሥልጣን ሊኖራቸው ይችላል? የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን የቤተክርስቲያኒቱን ባለሥልጣናት የቅዱሳት መጻሕፍት ተርጓሚዎች አድርገው ከፍ በማድረግ ይህንን ችግር ለመቋቋም ፈለገ። በዚህ ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እኩል ተደርጎ መታየት ጀመረ።

ይህንን ለቤተ ክርስቲያን ሥልጣን የተሰጠውንልዩ ሚና ለመረዳት በሁለት አቅጣጫዎች እንመለከታለን። በመጀመሪያ የመካከለኛው ዘመን የነገረ መለኮት ምሁራን ያለፈውን የቤተ ክህነት ባለሥልጣናትን እንዴት ተረዱ? ሁለተኛ የዘመኑን የመካከለኛው ዘመን ቤተክርስቲያን ባለሥልጣናትን እንዴት ተረዱ? ቀደም ብለን የቀድሞውን የቤተክርስቲያኗን ስልጣን እንመልከት።

### የቀደሙ ባለሥልጣናት

በተሃድሶው ዘመን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከቀድሞው ጀምሮ የቤተክርስቲያኒቱን ሥልጣን በበለጠ ዝርዝር አቀራረብ አዘጋጅታ ነበር። በርግጥ ቅዱሳት መጻሕፍት ራሳቸው የቤተ ክርስቲያን ቅርስ አካል ተደርገው ይታዩ ነበር። ሆኖም እኛ እንዳየነው በመካከለኛው ዘመን ፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች እራሳቸው በጣም ደብዛዛ ስለነበሩ ሌሎች የመመሪያ ምንጮች ያስፈልጉ ነበር። በዚህ ምክንያት የመካከለኛው ዘመን የነገረ -መለኮት ምሁራን ምን ማመን እንዳለባቸው ለመወሰን የቤተክርስቲያን ሥነ -መለኮትን ታሪክ ተመልክተዋል። እጅግ ብዙዎቹ የቤተክርስቲያኒቱን ታሪክ እንደ እግዚአብሔር ታሪክ ሕዝቡን በእውነት መንገድ እየመራ እንደሆነ አድርገው ተመልክተውታል። በዚህ ምክንያት ቀደም ሲል ቤተ ክርስቲያን ያስተማረችው ለመካከለኛው ዘመን የሃይማኖት ምሁራን ቢያንስ በሁለት መንገዶች በጣም አስፈላጊ ነበር።

በአንድ በኩል ለቀደሙት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ብዙ ትኩረት ተሰጥቷል። እንደ ፖሊካርፕ፣ ኢግናቲየስ፣ ኢሬናየስ፣ ተርቱሊያን እና ጀስቲን ሰማዕት የመሳሰሉት የወንዶች ጽሑፎች እና በኋላ እንደ አውግስቲን፣ አትናቴዎስ እና ጀሮም ያሉ

አባቶች በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የተለያዩ ትዕዛዞችን በጥልቅ ዳስሰዋል። አሁን እነዚህ አባቶች ብዙውን ጊዜ የማይሳሳቱ ተደርገው ይቆጠሩም ነበር፣ እናም የተለያዩ የቤተክርስቲያኑ ቅርንጫፎች የተለያዩ የአባታዊ ምክሮችን የመደገፍ አዝማሚያ ነበራቸው። ሆኖም ግን አሁንም በአብዛኛው እግዚአብሔር ለእነዚህ ታላላቅ የሃይማኖት ሊቃውንት ልዩ ግንዛቤዎችን እንደሰጣቸው እና ቤተክርስቲያን ለትምህርታቸው ልዩ ትኩረት መስጠት አለባት ተብሎ ይታሰባል። በመካከለኛው ዘመን የነበሩ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ከቤተክርስቲያኗ ቀደምት አባቶች አንድ ዓይነት ድጋፍ ሳይኖራቸው ምንም ዓይነት የሥነመለኮት አሳቦችን አያመነጩም ነበር፡፡

በሌላ በኩል የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያን እንደ ኒቂያ ጉባኤ ፣ የቁስጥንጥንያ ምክር ቤት እና የኬልቄዶን ጉባኤ ባሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ አጠቃላይ ሁሉን አቀፍ ጉባኤዎች ላይ የበለጠ ጥገኛ ነበር። የእነዚህ እና የሌሎች ጉባኤዎች ግኝቶች በጣም በቁም ነገር ተወስደዋል። ለሁሉም ተግባራዊ ዓላማዎች ፣ የመካከለኛው ዘመን የነገረ -መለኮት ምሁራን እነዚህን ግኝቶች እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማያጠራጥሩ ማጠቃለያ አድርገው ይቆጥሯቸው ነበር። ከእነርሱ ጋር አለመስማማት ከቅዱሳት መጻሕፍት እና ከክርስቶስ ጋር አለመስማማትን ያህል ነው።

መቶ ዘመናት ሲያልፉ ፣ ብዙ የአባቶች ትምህርቶች እና የእምነት ጉባኤዎች ግኝቶች ወደ ኦፊሴላዊ የቤተ -ክርስቲያን ወጎች አዳበሩ። እናም እነዚህ ወጎች እየጠነከሩ ሲሄዱ ፣ የቤተክርስቲያኑን ሰፊ ዶግማ ለማቋቋም ረድተዋል። ይህ የቤተ ክህነት ቀኖና እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት አንድ ዓይነት ሥልጣን የተሸከመ ሥነ -መለኮት እንጂ ሰው ፣ የማይወድቅ ሥነ -መለኮት ነው ተብሎ አይታሰብም። በእርግጥ ፣ ለሁሉም ተግባራዊ ዓላማዎች ፣ የቤተክርስቲያኑ ቀኖና ቅዱሳት መጻሕፍትን ተካ። ከተሐድሶው በፊት ታማኝ ክርስቲያኖች "መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?" ብለው መጠየቅ አይችሉም፤ ማለት የሚገባቸው "ቤተክርስቲያን ምን አለች?" የሚል ነበር፡፡



ከተሐድሶው በፊት የቤተ ክርስቲያኒቱ ቀኖና
ለሁሉም ተግባራዊ ዓላማዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ተካ።

የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን ለመረዳት ያለፉት የቤተ ክህነት ባለሥልጣናት አስፈላጊ እንደነበሩ ፣ በወቅቱ የቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ እንዲሁ ለዘመናዊ ሥነ -መለኮታዊ ባለሥልጣናት ከፍተኛ እይታን ፈጠረ።

### የዘመኑ ባለሥልጣናት

እርግጠኛ ለመሆን ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን በንድፈ ሀሳብ ማረጋገጧን ቀጥላለች። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ቀደም ሲል ባልተስተካከሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ቤተክርስቲያኗን ለመምራት በጣም ደብዛዛ ነበር። ስለዚህ አሁን ባለው ሥነ-መለኮታዊ ውዝግብ ውስጥ ቤተክርስቲያን እንዴት መመሪያን ማግኘት ነበረባት? በቀላል አነጋገር ፣ የመካከለኛው ዘመን የነገረ -መለኮት ምሁራን እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኗ ተዋረድ ውስጥ የሕያዋን ባለሥልጣናትን ሥርዓት እንደመሰረተ ያምኑ ነበር። እናም ይህ የሥልጣን ተዋረድ ለክርስቶስ አካል የማይጠራጠር ትምህርት ሰጥቶታል። የአሁኑን

ውዝግቦች የመፍታት ስልጣን በካህናት፣ በኤጵስ ቆጶሳት በሊቀ ጳጳሱ - ብዙዎች የማይሳሳቱ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆኑ በሚታሰቡት ላይ ነው። ሥነ -መለኮታዊ ውሳኔ መወሰን ሲያስፈልግ ፣ አማኞች "መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?" ብለው እንዲጠይቁ አልተበረታቱም። ይልቁንም "የቤተክርስቲያኒቱ ተዋረድ ምን ይላል?" ብለው እንዲጠይቁ ተደርገዋል።

> *በመካከለኛው ዘመን ፣ እነርሱ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በጣም ያሳስቧቸው ነበር ፣ ነገር ግን እነርሱ ከቅድመ-ወሳኝ ሥነ-አፈታትን ይከተሉ ነበር። በሌላ አገላለጽ ፣ የቤተ ክርስቲያን ወግ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ነው በሚለው መሠረታዊ እምነት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ይመጡ ነበር። አሁን ፣ እኛ እንደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ፕሮቴስታንቶች በዚህ ላይ ማሾፍ ለእኛ ቀላል ነው ፣ ግን እኛ ከዚህ ነፃ አይደለንም። የጆን ካልቪን ወይም ጆን ዌስሊ ወይም ማርቲን ሉተር ወይም ሌላ ሰው ትምህርት የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ነው የሚሉ ብዙ ወገኖቻችን አሉ። ስለዚህ በመካከለኛው ዘመናት እየሆነ የነበረው በእምነት አገዛዝ ላይ የተመሠረተ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመተርጎም የነበረ ጥረት ነው፡፡ የመካከለኛው ዘመን አስተርጓሚዎች እየጠየቁ ያሉት ጥያቄ "በሐዋርያት የተሰጠው እምነት በዚህ ምንባብ ዝርዝር መግለጫ ለእኛ እንዴት እየወጣ ነው?" የሚል ነው። ... ያለብን ችግር የቀደመችው ቤተክርስቲያን ወግን ባየችበት መንገድ እና በመካከለኛው ዘመን እና በባይዛንታይን ወግ ውስጥ እንደዚያ ዓይነት ሁኔታዎች በመኖራቸው ምክንያት... በተሃድሶው ውስጥ የተፈለገው ነገር የእምነት አገዛዝን እንደገና እንዴት መገንባት እንደሚቻል ነው... የተሐድሶ አራማጆች ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ የእምነትን አገዛዝ ለማስወገድ አላሰቡም። የእምነት አገዛዙ ትክክለኛ ቦታውን እንዲይዝ አስበው ነበር፡፡ ግን አብጦ ነበር፡፡*
>
> — *ዶ/ር ኬሪ ቪንዛንት*

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት ብቸኛው መንገድ በቤተክርስቲያን ባለሥልጣናት በኩል ከሆነ፣ ተራ ክርስቲያኖች ለመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ትኩረት የሚሰጡበት በቂ ምክንያት የለም። ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ሳይሆኑ የቤተ ክርስቲያኒቱ የሥልጣን ተዋረድ፣ የዘመኑ ሥነ -መለኮት የማይሳሳት መመሪያ ሆነ።

የመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክ እምነት አመለካከቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ አሁን የጥንት ፕሮቴስታንታዊ አመለካከቶችን ለማድነቅ ሁኔታ ላይ ደርሰናል። የመጀመሪያዎቹ ፕሮቴስታንቶች በሥነ -መለኮት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና የቤተ -ክርስቲያን ስልጣንን እንዴት ተረዱ?

## የመጀመሪያዎቹ ፕሮቴስታንቶች

ቀደምት ፕሮቴስታንቶች-እንደ ጃን ሁስ፣ ፒተር ዋልዶ፣ ጆን ዊክሊፍ እና ጊሮላሞ ሳቮናሮላ ያሉ የቅድመ ተሃድሶ ሰዎች ብለን የምንገልጻቸውን ጨምሮ-በዘመናቸው በቤተክርስቲያን ባለሥልጣናት የተፈጸሙ ብዙ በደሎችን አይተዋል። በቤተክርስቲያኗ ላይ የቅዱሳት መጻሕፍት ተግባራዊ ስልጣንን እንደገና በማረጋገጥ እነዚህን በደሎች ለመቅረፍ ሞክረዋል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ሰዎች ቋንቋዎች ተርጉመዋል። በብዛት መጽሐፍ ቅዱሶችን አሳትመዋል። ሰዎች ቅዱሳን መጻሕፍትን ማንበብ እንዲችሉ ማንበብና መጻፍ እንዲስፋፋ አድርገዋል። እናም የአከባቢው ፓስተሮች እና የተከተሏቸው ጉባኤዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ለራሳቸው እንዲያነቡ ያበረታቱ ነበር። ፕሮቴስታንቶች እነዚህ ጥረቶች በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን ሥነ -መለኮታዊ ችግር እንደማይፈታ ወዲያው ተረዱ። ነገር ግን የብሉይና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችን እና የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን በትክክል አረጋግጠዋል።

በመጀመሪያ ስለቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን የፕሮቴስታንት አመለካከትን እንመለከታለን። ከዚያ ስለ ቤተክርስቲያን ስልጣን የፕሮቴስታንት አመለካከት እንመረምራለን። እስቲ በመጀመሪያ ፕሮቴስታንት በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ላይ ያለውን አመለካከት እንመልከት።

### የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን

ቀደም ሲል እንዳየነው የመካከለኛው ዘመን የካቶሊክ አመለካከት በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ላይ በብዙ ጽንፈኛ አመለካከቶች ተስተጓጎለ። የጥንቶቹ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አራማጆች የቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ምሪት መጻፍ፣ ትርጉምን እና ግልፅነትን በማስተካከል ለእነዚህ ስህተቶች ምላሽ ሰጡ። በመጀመሪያ ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ምሪነት መጻፉን የሚመለከት ትምህርት እንመልከት።

## በመንፈስ ቅዱስ መነዳት

ገና ከመነሻው ልክ እንደ የመካከለኛው ዘመን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ተሐድሶ አራማጆች ቅዱሳት መጻሕፍት መለኮታዊም ሆነ የሰው አመጣጥ እንዳላቸው ተረድተዋል። በአንድ በኩል መጽሐፍ ቅዱስን ከአምላክ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ መጽሐፍ




ተሐድሶ አራማጆች ቅዱሳን መጻሕፍት ወደ እግዚአብሔር ሰዎች በመለኮታዊ አነሳሽነት እንደመጡ አረጋግጠዋል።

አድርገው ተመልክተውታል። ሉተር ፣ ዚዊንግሊ እና ካልቪን ፣ በማያሻማ ሁኔታ ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ እግዚአብሔር ሰዎች የመጡት በመለኮታዊ አነሳሽነት ነው እንደሆነ አረጋግጠዋል።
በ 2ጢሞቴዎስ 3:16 ላይ የሐዋርያው ጳውሎስን ቃል በቁም ነገር ይመለከቱታል -

> የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል። (2 ጢሞቴዎስ 3:16).

ይህ ምንባብ እንደሚያስተምር ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በመጨረሻ ከእግዚአብሔር የተገኙ ናቸው ፣ እናም እነርሱ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ የሆነ ልዩ መገለጥን ለመስጠት የተነደፉ ናቸው።

> የመንፈስ ቅዱስ መነሳሳት ፣ በሰፊው ትርጓሜ ፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ደራሲያን እግዚአብሔር በቃላት ለመናገር የፈለገውን በትክክል እንዲጽፉ የሚመራው መንፈስ ነው። ስለዚህ ሥነ-መለኮታዊ ቃሉ “መጋለጥ” ነው ፣ ማለትም ሰው ያለበት ሆኖ ግን መለኮታዊ የሆነ ነው፤ ሁለቱም መለኮትና ሰው አሉበት፡፡ በእርግጥ ያ ይለያያል። አንዳንድ ጊዜ መለኮታዊው በጣም ግልፅ ነው። ሌላ ጊዜ ሰው በጣም ግልፅ ይመስላል… ሆኖም ግን በትክክል እግዚአብሔር ያንን የሰው ደራሲ እየተጠቀመ ማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በመጀመሪያዎቹ ቅጂዎች እንዲጻፉ አድርጓል፡፡ ስለዚህ 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:16 የሚለው እግዚአብሔር

*በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንዲጻፉ እንዳደረገ ይናገራል ወይም የእግዚአብሔር ቃል "እግዚአብሔር የተነፈሰበት" መጽሐፍ ነው፡፡ በመንፈስ ተነድተው ጻፉ የሚለው ይህ ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት በዚህ ዐይነት ሁኔታ ተገኙ፡፡ ኃይል አለው፣ ፍፁም ነው ፤ በቃላት የተነገረ ነው። እንግዲህ በመለኮት ምሪት በመጻፉ ስህተት የለውም፡፡ በሁሉም መንገድ ልንታመንበት እንችላለን።*

— ዶ/ር ጄ ስኮት ሆረል

ተሐድሶ አራማጆች የእግዚአብሔር እጅ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከስህተት እንደጠበቀቻ ያምኑ ነበር። እግዚአብሔር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ስለአሁኑ ፣ ያለፈው እና ስለወደፊቱ መረጃ ከሰጣቸው በኋላ የጻፉት ሁሉ እውነት እንዲሆን ደራሲነታቸውን በበላይነት ተቆጣጠረ። ከሁሉም በላይ መለኮታዊ አነሳሽነት ቅዱሳት መጻሕፍትን ፍጹም፣ የማይጠረጠር ሥልጣን ሰጣቸው።

ነገር ግን የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አራማጆች የቅዱሳት መጻሕፍት ሰብዓዊ ደራሲዎች ለመጽሐፍ ቅዱስ ይዘት እና ትርጉም ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳደረጉ በመገንዘብ የመካከለኛው ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ስህተቶች አስወግደዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ከሰማይ እንደወረደ ከመቁጠር ይልቅ የጥንት ፕሮቴስታንቶች ቅዱሳት መጻሕፍት በሰው አማካኝነት እና በታሪካዊ ሂደቶች አማካይነት እንደመጡ አበክረው ተናግረዋል። ይህ የሰው ልጅ ደራሲነት ጉዳይ ኢየሱስ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ያስተናገዱበት መንገድ ጋር ይስማማል። ለምሳሌ ፣ በማቴዎስ 22: 41-44 ፣ ይህንን ዘገባ እናነባለን-

> ፈሪሳውያንም ተሰብስበው ሳሉ፥ ኢየሱስ። ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው? ብሎ ጠየቃቸው። የዳዊት ልጅ ነው አሉት። እርሱም። እንኪያስ ዳዊት። ጌታ ጌታዬን። ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው ሲል እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል?" (ማቴዎስ 22:41-44).

በዚህ ምንባብ ውስጥ ኢየሱስ የዚህን ምዕራፍ ጸሐፊ ዳዊትን በግልፅ በመሳብ ፈሪሳውያንን ለማደናገር መዝሙረ ዳዊት 110:1ን ተጠቅሟል። ኢየሱስም ሆነ ፈሪሳውያን መሲሑ የዳዊት ዘር እንደሚሆን ተስማምተዋል። ነገር ግን በመጀመሪያው መቶ ዘመን ፍልስጤም ውስጥ ዳዊት ዘሩን "ጌታ" ብሎ አይጠራውም ነበር። ስለዚህ ፣ ኢየሱስ ይህንን ማዕረግ ለልጁ የሰጠው ለምን እንደሆነ እንዲያብራሩ ፈሪሳውያንን ጠየቃቸው።

የኢየሱስ ክርክር የተመካው የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በከፊል በሰው ልጆች ደራሲዎች ሕይወት ውስጥ በዝርዝር ላይ በመመሥረቱ ላይ መሆኑን ልብ በሉ። እንደዚህ ያሉ ምሳሌዎች ሙሴ፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ዳዊት፣ ጳውሎስ እና ሌሎች የእግዚአብሔር ቃል መሣሪያዎች የሚያመለክቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች እና ገጸ-ባህሪዎች በብዛት አሉ። እነዚህ የሰው መሣሪያዎች ለቅዱሳን መጻሕፍት ጉልህ የሆነ የግል አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

ከእነዚህ እና ከሌሎች ምሳሌዎች፣ ተሐድሶ አራማጆች ቅዱሳን መጻሕፍት ከእውነተኛው ሰብዓዊ ሁኔታዎች ተነስተዋል ብለው በትክክል መደምደማቸው ነው፡፡ እነርሱ በልዩ ታሪካዊ ሁኔታዎች በሰዎች የተፃፉ ናቸው፡፡ ክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል ቢረዱ፣ የቅዱሳት መጻሕፍትን መለኮታዊ አመጣጥ ብቻ ሳይሆን ሰብአዊ፣ ታሪካዊ አመጣጣቸውን ማጉላት አለባቸው።

የጥንቶቹ ፕሮቴስታንቶች በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ላይ ያላቸው አመለካከት ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ አነሳሽነት መለኮታዊም ሆነ ሰብዓዊ ጎኖች ክብደትን ሰጣቸው። እናም ይህ በመነሳሳት ላይ ያለው አመለካከት ተሐድሶ አራማጆች የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም በጻኑበት መንገዶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል።

## ትርጉም

የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉምን ቀደምት የፕሮቴስታንት አቀራረብን በዚህ መንገድ ማጠቃለል እንችላለን - በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተደበቁ መለኮታዊ ትርጉሞችን በመፈለግ የመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክን ሞዴል ከመከተል ይልቅ ትርጓሜዎቻቸውን በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ቀጥተኛ ትርጉም ውስጥ ለመጣል ፈለጉ። . በቀላል አነጋገር ፣ እነርሱ ያተኮሩት የሰው ጸሐፊዎች ከዋና ተደራሲያን ጋር ለመገናኘት ባሰቡት ትርጉም ላይ ነው።

አሁን የጥንት ፕሮቴስታንቶች የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጉም ሙሉ በሙሉ ከመካከለኛው ዘመን አቀራረቦች ጋር እንዳልጣሱ ማወቅ አለብን። አንዳንድ ጊዜ የጥንታዊ (polyvalence) ጥቅሶች - ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ የትርጉም ደረጃዎች አሏቸው የሚለው እምነት - በተሐድሶ ጽሑፎች ውስጥ ታይቷል። ለምሳሌ ፣ ሉተር በመዝሙራት ላይ የሰጠው አስተያየት በዚህ የትርጓሜ ዘዴ ላይ ቀጣይ ጥገኝነት ያሳያል። ያም ሆኖ ተሐድሶ አራማጆች ከብዙዎቹ የካቶሊክ ባልደረቦቻቸው ይልቅ በሰው ደራሲ የታሰበበት ትርጉም ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠታቸው ተገቢ ነው። እናም በአብዛኛዎቹ ብዙ የቅዱስ ጽሑፋዊ ምንባቦቻቸውን አተገባበር በጽሑፉ የመጀመሪያ ትርጉም መሠረት አደረጉ።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ቃል በቃል ወይም ግልጽ ትርጉም ላይ ቀደምት የተሐድሶዎች አፅንዖት ለመረዳት ፣ አንዳንድ ታሪክን ማስታወስ ይረዳል። ይህ የሥነ-አፈታት ወይም የቅዱሳት መጻሕፍት የአተረጓጎም አቀራረብ በምዕራብ አውሮፓ በ15ኛው ክፍለ ዘመን ህዳሴ በኩል ሥር ሰድዶ ነበር። ህዳሴው ወይም "ዳግም መወለድ" ስሙን ያገኘው ከጥንታዊው ሮማን እና በተለይም ከግሪክ ሥነ ጽሑፍ እና ባህል ከተሃድሶው በፊት በምዕራብ አውሮፓ ከተከናወነው ፍላጎት ነው። ከህዳሴው በፊት ምሁራን በጥቅሉ የግሪክን ጥንታዊ ጽሑፎች በትርጉም ብቻ ያውቁ ነበር። እናም የእነዚህ ጽሑፎች ትርጓሜዎች በአብዛኛው በቤተ ክርስቲያን ቁጥጥር ሥር ነበሩ። በተለያዩ ጊዜያት ቤተክርስቲያኑ ፕላቶ፣ አርስቶትል እና ሌሎች የግሪክ ጸሐፊዎችን ሆን ብለው የክርስትናን ትምህርት በሚደግፉ መንገዶች ተርጉማ ነበር። ነገር ግን በሕዳሴው ዘመን፣ ብዙ ሊቃውንት ከቤተክርስቲያናዊ ቁጥጥር ነፃ ሆነው የጥንታዊውን ዘመን ጽሑፎች ለመረዳት ፍላጎታቸውን የሚደግፉ ደንበኞችን አግኝተዋል። ደራሲዎቻቸው መጀመሪያ እንዲረዱት እንደፈለጉ እነዚህን ጽሑፎች መተርጎም ጀመሩ። እናም በውጤቱም ፣ በጣም የተከበሩ የጥንታዊ ሥነ-ጽሑፍ ትርጓሜዎች በታሪካዊ ትርጉማቸው ላይ ማተኮር ጀመሩ-ይህ ትርጉም ብዙውን ጊዜ ከቤተክርስቲያን አስተምህሮዎች ጋር በእጅጉ ተቃራኒ ነበር።*

*አሁን እንዲሁም በሕዳሴው ዘመን ፣ የዕብራይስጥ እና የግሪክ መጽሐፍ ቅዱሶች አዲስ እትሞች ታትመዋል። ይህ በቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ውስጥም ጉልህ ለውጥ እንዲኖር አድርጓል። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ፣ ከእነዚህ ቀናት በፊት ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባቦች በአብዛኛው የተተረጎሙት በቤተክርስቲያን መሪነት እና በቤተክርስቲያን ቀኖና ድጋፍ ነው። ነገር ግን የሕዳሴውን መርሆዎች በመከተል ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት - በተለይም ፕሮቴስታንቶች - ከቤተ ክርስቲያን ቁጥጥር ነፃ የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ ጀመሩ። የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜዎች በመጀመሪያው ታሪካዊ ትርጓሜ መሠረት ለማድረግ ፈልገው ነበር። ይህ የፕሮቴስታንት ዝንባሌ ወደ መጀመሪያው ትርጉሙ - ወይም "ቃል በቃል ስሜት" - የሁሉም ትርጓሜ መሠረት እንደመሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም በመረዳት ረገድ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል። ፕሮቴስታንቶች አሁን ስለ እያንዳንዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ አንድ ወጥ የሆነ የሆነ ትርጉም መናገር ጀመሩ፡፡*

የዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫ ምዕራፍ 1 ፣ ክፍል 9 እንዲህ ይላል -

**የማንኛውም የቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኛ እና ሙሉ ስሜት… ብዙ አይደለም ፣ ግን አንድ ነው፡፡**

ይህንን አመለካከት ለትርጉም "ያልተለመደ" ብለን ልንጠራው እንችላለን።

በእርግጥ ፣ ቀደምት ፕሮቴስታንቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ብዙውን ጊዜ ቃል በቃል በቀላሉ ከመገምገም የበለጠ እንደሚናገሩ ተገንዝበዋል። ከዋናው የሰው ልጅ ጸሐፊዎች ግንዛቤ በላይ ከሚሆኑ ከክርስቲያናዊ እውነቶች ጋር ብዙ እንድምታዎች እና ግንኙነቶች ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ገጽታዎች አሁንም የነጠላ፣ እውነተኛ እና ሙሉ ትርጓሜ አካል ናቸው ምክንያቱም እነርሱ ከቅዱሳን ጽሑፎች ቃል በቃል ወይም ግልጽ ስሜት ጋር ይጣጣማሉ።

> *እኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ ስንሠራ ፣ በእውነት የምንከተለው በጽሑፉ ውስጥ ቃል በቃል የሚሆነውን ነው። በሌላ አነጋገር ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ጸሐፊ - እኛ ሆሴዕን ወይም ሐዋርያው ጳውሎስን እያወራን - ያ ጸሐፊ በአጠቃላይ ምን ለማሰብ ፈለገ? ጸሐፊው ለመናገር የፈለገውን በትክክል ለማግኘት ሁሉን አቀፍ በሆነ መንገድ ወደ ጸሐፊ አእምሮ ውስጥ መግባት ይከብዳል፡፡ እኛ ልንከታተለው የሚገባው አንድ ነገር ቢኖር ፣ እኔ እንደማምነው፣ ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ባለሁለት ጸሐፊ መሆናቸውን ነው፡፡ ሁሉም በእግዚአብሔር እና በሰው የተጻፉ ናቸው። ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ያላሰቡበትን መንፈስ ቅዱስ ሁለተኛ ፣ ሦስተኛ ፣ አራተኛ ትርጓሜዎች ያላቸውን እንዲጽፉ አድርጎ ሊሆን ይችላል፡፡ የመጀመሪያው ጸሐፊ እንኳ ሙሉ በሙሉ አያውቅም ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን እግዚአብሔር ያንን ይጠቀማል። እኔ በጣም አስፈላጊው ወደ ጽሑፉ ቀጥተኛ ትርጉም መመለስ ይመስለኛል። ያ ሌሎች ሁሉም ቀጣይ የትርጉም ንብርብሮች የሚመሰረቱበት መልህቅ ነው።*
>
> — ኒኮላስ ፔሪን ፣ ፒኤችዲ

*የጥንቶቹ ፕሮቴስታንቶች ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መጻፋቸው ውስጥ ሰብዓዊ ድርሻን እና የቅዱሳት መጻሕፍትን አንድነት አስፈላጊነት ከማጉላት በተጨማሪ የቅዱሳት መጻሕፍትን ግልፅነት በመጠበቅ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን ለማጽናት ይፈልጉ ነበር።*

## ግልጽነት

ተሐድሶ አራማጆች ቅዱሳት መጻሕፍትን እንደ ድብቅና ሥልጣን ያለው የቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ እንደሚያስፈልጋቸው ከማየት ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ ለመረዳት የማያስቸግር እንደሆነ ሞግተዋል። በርካታ ምክንያቶች ለፕሮቴስታንት የመጽሐፍ ቅዱስ ግልፅነት አስተምህሮ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ የሚንቀሳቀስ ተንቀሳቃሽ ዓይነት ማተሚያ በስፋት ጥቅም ላይ መዋሉ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሶች እንዲኖሩ አድርጓል። መጽሐፍ ቅዱሶች መገኘታቸው ደግሞ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን በራሳቸው እንዲያነቡ አስችሏቸዋል። ይህን ሲያደርጉ የካቶሊክ ቤተክርስትያን ቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽ እንዳልሆኑ ሲያውጅ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለመገምገም ችለዋል።

በሁለተኛ ደረጃ ደፋር ፈር-ቀዳጆች ቅዱሳን መጻሕፍትን ወደ ተራ ሰዎች ቋንቋ መተርጎም ጀመሩ። ይህ ደግሞ ሰዎች የቅዱሳት መጻሕፍትን ግልፅነት ለራሳቸው እንዲመረምሩ አስችሏቸዋል።

በሦስተኛ ደረጃ ፣ የተሐድሶ አራማጆች ትኩረት በቃል ትርጉም  እንዲሁም የነገረ-መለኮት ሊቃውንት ትርጓሜያቸውን ሊመረመር በሚችል ነገር ላይ እንዲመሰረት አስችሏል። መጽሐፍ ቅዱስ ምን ማለት እንደሆነ በመንገር በቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ላይ ብቻ መተማመን አያስፈልጋቸውም። በእነዚህ መንገዶች የቅዱሳት መጻሕፍት ምርመራ ከካቶሊክ አመለካከት በተቃራኒ መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ግልፅ መሆኑን በሰፊው እንዲገነዘብ ምክንያት ሆኗል።

እነዚህ እድገቶች ፕሮቴስታንቶች የመጽሐፍ ቅዱስን ግልፅነት የሚያረጋግጡበት እና መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ተግባራዊ ስልጣን ወደ ክርስትና እንዲመልሱ መንገድ ከፍተዋል። በዚህ አዲስ ሁኔታ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንደ ተደበቀባቸው የወሰዷቸው ብዙ ወሳኝ ምንባቦች በእውነቱ በአንፃራዊነት ለመረዳት ቀላል እንደሆኑ ግልፅ ሆነ፡፡ የፕሮቴስታንት አስተርጓሚዎች ብዙ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያጠኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች በሚያስደንቅ ሁኔታ ግልፅ ሆነው ታዩ።

> *ማርቲን ሉተር በአንድ ወቅት በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በሮሜ መጽሐፍ ላይ ሲያስተምር ነበር ፣ እና በትምህርቶቹ ወቅት ያገኘው አንድ ጥቅስ ሕይወቱን በግሉ ብቻ ሳይሆን በእውነቱ የእኛ የክርስትናን ገጽታ ለውጦታል። ማርቲን ሉተርን እንዲህ ያደረገው ጥቅስ ሮሜ 1:17 ነበር ፣ እና ያ ጥቅስ በቀላሉ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ይላል። በዚያን ጊዜ ቤተክርስቲያኑ አንድ ሰው በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ሊያከናውናቸው የሚገባቸው ቅዱስ ቁርባኖች እንዳሉ ታስተምር ነበር ፣ ይህም ከጊዜ በኋላ ጸጋን ለመቀበል ያስችላል፣ እናም በእግዚአብሔር ፊት ወደ ትክክለኛው ደረጃ ትደርሱ ይሆናል። ነገር ግን ይህ ጥቅስ ያስተማረው ሉተር ተረድቶ ነበር ፣ ክርስቶስን በእምነት ስንቀበል ፣ ወዲያውኑ በልዑል እግዚአብሔር ፊት ጽድቅን ሆኖ ይቆጠርልናል። በእርግጥ እኛ መልካም ሥራዎችን መሥራት እና እግዚአብሔርን ለማገልገል ነገሮችን ማድረጋችንን መቀጠል እንፈልጋለን - ጻድቅ እንድንሆን ሳይሆን በክርስቶስ በማመን ብቻ ጻድቅ ስለሆንን ነው።*
>
> — ቄስ ጆርጅ ሻምብሊን

አሁን ፣ በተሃድሶው የመጀመሪያዎቹ አስርት ዓመታት ውስጥ ፕሮቴስታንቶች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ግልፅነት በጣም ብሩህ አመለካከት ነበራቸው። ሁሉም ቀለል ያለ ጉዳይ ይመስል ነበር - መጽሐፍ ቅዱስን ያንብቡ እና ሥነ -መለኮትን እዚያ ከተገኘው የእግዚአብሔር ግልፅ መገለጥ ጋር ያስተካክሉ። ነገር ግን የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ በቅዱሳን ጽሑፎች መስራቱን ሲቀጥል ፣ ፕሮቴስታንቶች ራሳቸው የበለጠ ከተጨባጭ ነባራዊ እውነታ ጋር መሄድ ጀመሩ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልፅነት ደረጃዎች መናገር ጀመሩ። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ከሌሎቹ ይበልጥ ግልጽ እንደሆኑ ግልጽ ሆነ። ስለዚህ ሉተራኖች ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ምንባብ አንድ ነገር ሲያምኑ፣ ካልቪኒስቶች ሌላ፣ ዚንግሊያንስ ደግሞ ሌላ ፣ የቀደመው፣ በተስፋ-የተሞላው መጽሐፍ ቅዱስ ግልፅ ነው የሚለው አመለካከት የበለጠ ብቃት ላላቸው አመለካከቶች ቦታ ሰጠ። ይህ የበሰለ የፕሮቴስታንት አመለካከት ሊያስገርመን አይገባም። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንኳ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ አንዳንድ ነገሮች ለመረዳት አስቸጋሪ እንደሆነ አምኗል። በ 2ጴጥሮስ 3:16 ላይ ጴጥሮስ እነዚህን ቃላት ጽፏል፡-

> በእነዚያ ዘንድ ለማስተዋል የሚያስቸግር ነገር አለ፥ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ። (2 ጴጥሮስ 3:16).

ጴጥሮስ እንዴት እንዳስቀመጠው ልብ በሉ። የጳውሎስ ጽሑፎች ሁሉ ለመረዳት ቀላል እንደነበሩ አልተናገረም። ወይም ሁሉም ለመረዳት አዳጋች አልነበሩም። ከዚህ ይልቅ በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ አንዳንድ ነገሮች ለመረዳት አዳጋች እንደሆኑ ተናግሯል።



ተሐድሶ አራማጆች መጽሐፍ ቅዱስን በቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ላይ ከፍ አድርገውታል።

ስለዚህ ከመካከለኛው ዘመን ቤተክርስቲያን በተቃራኒ፣ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አራማጆች መጽሐፍ ቅዱስን በቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ላይ ከፍ ከፍ አደረጉ። ፕሮቴስታንቶች በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከእግዚአብሔር መገለጥ እንዳልተቆረጡ ተረዱ። እነርሱ የቅዱሳት መጻሕፍትን ግልፅነት አረጋግጠዋል፣ በዚህም ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉም የቤተ ክህነት ሥልጣን ላይ ፍጹም ባለሥልጣን ሆኖ ተመልሷል።

*የተሐድሶ አራማጆች ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን ተገንዝበው ፣ እኛ በተፈጥአችን የእግዚአብሔርን ነገሮች ወስደን ለማዛባት፣ ለመቀነስ እና ተገቢ ባልሆነ መንገድ የመተግበር ዝንባሌ እንዳለን ተረድተዋል። እናም በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያንን መስክረዋል፡፡ ያ በእርግጥ ከሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ትምህርቶች ጋር ብዙ ግጭታቸውን አፋጠነው። እናም የእግዚአብሔር ቃል ስልጣን የመጨረሻው ስልጣን መሆን እንዳለበት የእነርሱ ጽኑ እምነት ነበር። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ እና እስከ ዛሬ ድረስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከፍተኛው ሥልጣን መሆኑን ብትስማማም፣ ቤተክርስቲያኗ ቅዱሳት መጻሕፍትን የመተርጎም ሥልጣን እንዳላት ታምናለች፡፡ በእርግጥ የመጨረሻው ስልጣን እንዳላት ታምናለች፡፡ እዚያ ያለው አደጋ ሰዎች ኃጢአተኞች ናቸው። የተሐድሶ አራማጆች በዚያን ጊዜ እንደተረዱት ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለመጫን የሚፈልግ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር መኖሩ ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ የእግዚአብሔር ቃል ለኃጢአተኛ ሰው ወይም ለኃጢአተኛ ስብስብ ትርጓሜ እንዲገዛ ማድረግ በመሆኑ እጅግ አደገኛ ነው፡፡ ስለዚህ ለተሐድሶ አራማጆች እና ለእኛ ማንኛውም ነገር ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መስማማት እና ለእግዚአብሔር ቃል መገዛት የግድ አስፈላጊ ነው።*

— ዶ/ር ስቲቭ ኩርቲስ

አሁን በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ላይ የመጀመሪያውን የፕሮቴስታንት አመለካከት ከተመለከትን፣ ቀደምት ፕሮቴስታንቶች የቤተክርስቲያኗን ሥልጣን እንዴት እንደተመለከቱ ለማየትም እንሞክራለን፡፡

## የቤተክርስቲያን ሥልጣን

የቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መጻፍ፣ ትርጉምና ግልፅነት የፕሮቴስታንት ዕይታዎች ቀደምት ፕሮቴስታንቶች በቤተክርስቲያን ባለሥልጣናት ላይ ብቸኛው የማይጠረጠር የእምነት እና የሕይወት መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲመልሱ አስችሏቸዋል። እንደ ወንጌላውያን ፣ እኛም ዛሬ እንዲሁ ማድረግ አለብን። አሁንም አንድ አስፈላጊ መመዘኛ ማከል አለብን። የመጀመሪያዎቹ ፕሮቴስታንቶች የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን እስካረጋገጡ ድረስ የነገረ-መለኮት ትምህርታቸውን ሲገነቡ ሁሉንም የቤተክርስቲያኒቱን ሥልጣን ሙሉ በሙሉ አልተቀበሉም። በተቃራኒው ፕሮቴስታንቶች እግዚአብሔር ለማይሳነው የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች በመገዛት እግዚአብሔር በሁለተኛ ደረጃ የማይወድቅ ሥልጣንን ለቤተ ክርስቲያን እንደሰጠ ያምኑ ነበር።

ስለቤተክርስቲያን ስልጣን የፕሮቴስታንት አመለካከት ለመዳሰስ በሁለት አቅጣጫ ማየት ይረዳል። በመጀመሪያ ፣ የጥንት ፕሮቴስታንቶች ያለፈውን የቤተ ክህነት ባለሥልጣናትን እንዴት ተረዱ? እና ሁለተኛ ፣ የዘመናቸውን የፕሮቴስታንት ባለሥልጣኖቻቸውን እንዴት ተረዱ? በመጀመሪያ የጥንት ፕሮቴስታንት በቤተክርስቲያናዊ ስልጣን ላይ ያለውን አመለካከት እንመልከት።

## የቀደሙ ባለሥልጣናት

ምንም እንኳን ለብዙዎቻችን መገመት ከባድ ቢሆንም ቀደምት ፕሮቴስታንቶች በቤተክርስቲያን አባቶች እና በቀደሙት የቤተክርስቲያን ጉባኤዎች ትምህርቶች ውስጥ ትልቅ ስልጣን እውቅና ሰጥተዋል። ተሐድሶ አራማጆች ጠንካራ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጠብቀዋል። መንፈስ ቅዱስ የጥንቷን ቤተ ክርስቲያን በዘመናቸው በክርስቲያኖች ዘንድ እውቅና ሊሰጣቸው ወደሚገባቸው ብዙ አስፈላጊ እውነቶች እንደመራቸው አጥብቀው ያምኑ ነበር።

ቀደም ባለው ትምህርት ውስጥ እንደጠቀስነው ፣ ተሐድሶ አራማጆች በቅዱሳት መጻሕፍት ስልጣን በሶላ ስክሪፕተራ - “ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ” ስር ሆነው ይናገሩ ነበር። እንደ አለመታደል ሆኖ ዛሬ ብዙ ወንጌላውያን ስለ ሶላ ስክሪፕቱራ አስተምህሮ ከባድ የግንዛቤ ችግር አላቸው። በዘመናችን ብዙ ወንጌላውያን የሶላ ስክሪፕቱራ አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ምንም ሥልጣን ሊኖረን አይገባም ብለው ያምናሉ። ግን ይህ የተሐድሶው አቋም አልነበረም፡፡ የሶላ ስክሪፕቱራ አስተምህሮ እውነተኛ አንድምታ ይህ አይደለም። የተሐድሶ አራማጆች በሶላ ስክሪፕቱ ላይ አጥብቀው ይከራከራሉ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የአማኞች ብቸኛ ሥልጣን ነው ብለው ስላመኑ አይደለም። ይልቁንም ለአማኞች የማያከራክር ሥልጣን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ማለታቸው ነው። ምንም እንኳን እንግዳ ቢመስልም ፣ ፕሮቴስታንቶች ሌሎች ሁሉንም ባለሥልጣናት ከእጃቸው ስላሰናበቱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሚለውን ዶክትሪን በጥብቅ አልጠበቁም። ሌሎች ሥነ-መለኮታዊ ሥልጣናትን ከፍ አድርገው ስለያዙ በትክክል ተሚግተውለታል።

> *በተሃድሶ አራማጆች ውስጥ በተለይም በካልቪን ውስጥ ከሚትመለከቱት ነገሮች አንዱ በሶላ ስክሪፕቶራ እምነት - ወይም የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን የቤተክርስቲያን መሠረት ነው የሚል እምነት - እና ለእምነት አባቶች ባላቸው አክብሮት መካከል መሠረታዊ ግጭት አለማየታቸው ነው። እነርሱ በአባቶች ልብ ውስጥ እንደነበረው ቤተክርስቲያንን ወደ ቀደምት፣ ንፁህ ወግ እንደ መለሱ ይመለከቱ ነበር… እናም እነርሱ የመጽሐፍ ቅዱስን ግንዛቤያቸውን በቤተክርስቲያን ወግ ለመደገፍ ፈልገው ነበር ፣ ስለሆነም በእውነቱ እንደ መሠረታዊ ተፎካካሪ መርሆዎች አላዩአቸውም። ነገር ግን እነርሱ እንዲሁ የቤተክርስቲያን ወግ እና የጥንት የቤተክርስቲያን አባቶች ስልጣንን እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ስልጣን በተመሳሳይ ደረጃ ላይ አላስቀመጡም።*
>
> — ዶ/ር ጀፍ ድሪደን

ለግንዛቤ ሲባል በዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫ ምዕራፍ 1 ክፍል 10 ውስጥ የእነዚህን ጉዳዮች ማጠቃለያ ማመልከት ጠቃሚ ነው።

> *ሁሉም የሃይማኖት ውዝግቦች የሚወሰኑበት እና ሁሉም የጉባኤዎች ድንጋጌዎች ፣ የጥንት ጸሐፊዎች አስተያየት ፣ የሰዎች ትምህርቶች እና የግል መናፍስት የሚመረመሩበት ከፍተኛ ዳኛ ፣ እና በየትኛው ዓረፍተ -ነገር ውስጥ ማረፍ እንዳለብን የሚያሳየን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከሚናገረው ከመንፈስ ቅዱስ በቀር ምንም ሊሆን አይችልም።*

ይህ አንቀጽ በቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ “የሃይማኖት ክርክሮች ሁሉ የሚወሰኑበት ከፍተኛ ዳኛ” መሆኑን በጥብቅ ያረጋግጣል። በሌላ አነጋገር የቤተክርስቲያን ፍርድ ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት መስፈርት መሠረት መደረግ አለበት። ግን እዚህ ቋንቋውን ልብ በሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ “ከፍተኛው ዳኛ” ነው። አሁን ፣ አንድ ነገር ከፍተኛው ዳኛ ከሆነ ፣ የበላይ ያልሆኑ ሌሎች ዳኞች መኖራቸውን ልብ በሉ። በእርግጥ ፣ መግለጫው በዚህ ምንባብ ውስጥ ሌሎች በርካታ ሥልጣናትን ጠቅሷል። አስፈላጊ ቅደም ተከተል በሚመስለው ውስጥ ጉባኤዎችን ይጠቅሳል ፤ የጥንት ጸሐፊዎች ፣ ወይም የቤተክርስቲያን አባቶች; ቀደም ባሉት ጊዜያት እና አሁን በቤተክርስቲያን ውስጥ የሌሎችን ትምህርት፣ የሰዎች ትምህርቶች ፣ እና የግል መናፍስት ማለትም አንድን ጉዳይ በተመለከተ ውስጣዊ ስሜት ወይም እምነት ያላቸውን - ይጠቅሳል። የዌስትሚኒስተር መግለጫ ለእነዚህ ባለሥልጣናት እውቅና ሰጥቷል ፣ ግን ሁለተኛ ደረጃን ሰጣቸው - በቅዱሳት መጻሕፍት ፍጹም ሥልጣን ሥር እንዲሆኑ አድርጓል።

አሁን የካቶሊክ የሃይማኖት ሊቃውንት ተሐድሶ አራማጆች የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥልጣን ባለመቀበል ይከሷቸዋል። ነገር ግን ተሐድሶ አራማጆች የመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አስተምህሮአቸውን ጠብቀው በመቆየታቸው ያለፈውን ላለመቀበል መጠንቀቅ ነበረባቸው። ቀደምት ፕሮቴስታንቶች ብዙውን ጊዜ ሐሳባቸውን የሚደግፉት ከቀደምት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጋር በማጣቀስ ነበር። በእውነቱ ፣ በእያንዳንዱ የጆን ካልቪን የክርስትና ሃይማኖት መዋቅር በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ካልቪን ከቀደሙት የቤተክርስቲያን አባቶች ጋር የበለጠ መስተጋብር አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በካልቪን መጽሐፍ ውስጥ አንድ



ቪዲዮዎችን፣ የትምህርት መመሪያዎችና ሌሎች ግብዓቶችን ለማግኘት Thirdmill at thirdmill.org. ይመልከቱ.

ምንባብ በቤተክርስቲያኗ ጉባኤዎች ሥልጣን ላይ ያለውን አመለካከት በግልጽ ያሳያል። ካልቪን በክርስትና ሃይማኖት መዋቅር መጽሐፉ 4 ምዕራፍ 9 የተናገረውን ያዳምጡ

> እኔ እዚህ የምከራከረው ሁሉም ጉባኤዎች ሊወገዙ ወይም የሁሉም ድርጊቶች መሻር አለባቸው ፣ እና (ቃሉ እንደሚለው) በአንድ ምት መሰረዝ አለባቸው በማለት አይደለም። ነገር ግን ፣ እያንዳንዱ ሰው ጉባኤዎቹ የሚወስኑትን የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት እንዲኖረው ሁሉንም ነገር ማዋረድ አለባችሁ ትላላችሁ። አይደለም! ነገር ግን የማንኛውም ጉባኤ አዋጅ በቀረበ ቁጥር በመጀመሪያ በየትኛው ጊዜ እንደተካሄደ፣ በምን ጉዳይ እንደተወያየ እና በየትኛው ዓላማ ፣ ምን ዓይነት ሰዎች እንደተገኙ ማሰላሰልና መመርመር እፈልጋለሁ። ከዚያም ያከናወነውን በቅዱሳት መጻሕፍት መመዘኛ ለመመርመር እፈልጋለሁ፡፡ ይህን ለማድረግ የጉባኤውን ትርጉም የራሱ የሆነ ሚዛን ይኖሯል - ጊዜያዊ ፍርድ- ግን እኔ የጠቀስኩትን ዐይነት ምርመራ ማደናቀፍ የለበትም፡፡

በካልቪን ቃላት ውስጥ በርካታ አስፈላጊ ሀሳቦች እዚህ ጎልተው ይታያሉ። በመጀመሪያ ፣ የቤተክርስቲያን ጉባኤዎች በታሪክ መረዳት እንደሚገባ አጥብቆ አሳስቧል። እነርሱ ጊዜ የማይሽራቸው፣ በቀጥታ ከእግዚአብሔር የተገለጡ አልነበሩም። የህዳሴው የትርጓሜ ዘዴዎች-ቃል በቃል-ታሪካዊ ስሜት ላይ ያተኮረ-በቤተክርስቲያን ጉባኤዎች ላይ መተግበር አለበት። አማኞች "በየትኛው ጊዜ [ጉባኤ] እንደተካሄደ ፣ በምን ጉዳይ ላይ ፣ እና በየትኛው ዓላማ ፣ ምን ዓይነት ሰዎች እንደነበሩ" ማሰላሰል አለባቸው።

ሁለተኛ ፣ የሶላ ስክሪፕቱራ ዶክትሪን ካልቪን የቤተክርስቲያኒቱ ትምህርቶች በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት መገምገም እንዳለባቸው አጥብቆ እንዲያስብ አደረገው። እሱ እዚህ እንዳስቀመጠው "የቅዱሳት መጻሕፍት መመዘኛ" መተግበር አለበት።

ነገር ግን ሦስተኛ ፣ እና ከሁሉም በላይ እዚህ ዓላማችን ካልቪን ያለፈው ትምህርቶች "እንደ ጊዜያዊ ፍርድ" መቀበል እንዳለባቸው ተናግሯል። ያም ማለት ፣ የቤተክርስቲያኗ የረጅም ጊዜ ፣ የጥንት ግኝቶች እንደ ጊዜያዊ ወይም የመጀመሪያ ፍርዶቻችን ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል። ጥንቃቄ የተሞላበት፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ ስህተት መሆናቸውን እስኪያረጋግጥ ድረስ ትምህርታቸውን መቀበል አለብን።

የካልቪን ስትራቴጂ በዘመኑ በጣም አክራሪ ከሆኑት ፕሮቴስታንቶች በስተቀር ሁሉንም የሚመራውን ጥበብ ያንፀባርቃል። እጅግ በጣም ብዙ ፕሮቴስታንቶች ለቀደሙት የቤተክርስቲያን አባቶች እና ለቤተክርስቲያኗ የሃይማኖት መግለጫዎች እውቅና ሊሰጣቸው የሚገባውን ከፍተኛ ስልጣን ተረድተዋል። ለቅዱሳት መጻሕፍት የበላይነት ቁርጠኝነት በማሳየት እነዚህ ያለፉ የቤተክርስትያን ሥልጣናትን አስተናገዱ፡፡

ቀደምት ፕሮቴስታንቶች የቤተክርስቲያን ስልጣን ከቀደሙት የቤተ ክህነት ባለሥልጣናት ጋር በተያያዘ እንዴት እንደተመለከቱ ከተመለከትን ፣ ተሐድሶ አራማጆች የራሳቸውን የዘመኑ የፕሮቴስታንት ባለሥልጣናትን እንዴት እንደተረዱት ማየት አለብን፡፡ የአሁኑን ሥነ-መለኮታዊ ጭንቀቶች ለመመለስ ሲፈልጉ ለራሳቸው እና ለሌሎች ምን ዓይነት ስልጣን ሰጥተዋል?

### የዘመኑ ባለሥልጣናት

እንደምታስታውሱት የመካከለኛው ዘመን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የማይሻር ጳጳስ እስከሚሆን ድረስ የተራቀቀ ሕያው ሥነ-መለኮታዊ ባለሥልጣናትን ሥርዓት አዘጋጅታ ነበር። የፕሮቴስታንት ተሐድሶ በአብዛኛው ይህንን የቤተ ክህነት ሥልጣን አልተቀበለም ነበር። የማይጠራጠር ሆኖ ተቀባይነት ማግኘት ያለበት የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ብቻ ነበር ብለው ተቃወሙ። ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳቱ ፣ የቤተክርስቲያኑ ጉባኤዎችሽእና ሌሎች የቤተ ክህነት ባለሥልጣናት የሚሳሳቱ እና ለስህተት የተጋለጡ ነበሩ።

አሁን ፣ ቀደምት ፕሮቴስታንቶች በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በትክክል የተሾሙ መምህራንን ስልጣን በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያከብሩ መረዳት አስፈላጊ ነው። ፕሮቴስታንቶች የተሃድሶ ሥነ -መለኮትን የበለጠ ሲያሳድጉ ፣ የግለሰቡ ሊቃውንት ወይም "የቤተክርስቲያኗ ዶክተሮች" ከፍተኛ ክብር ይገባቸዋል። እንደ እውነቱ ከሆነ ፣ በሁሉም ቤተ እምነቶች ውስጥ ፕሮቴስታንቶች በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እንደ ሁለተኛ ባለሥልጣናት እውቅና የተሰጣቸውን የእምነት ቃላትን ፣ ካቴኪዝምን እና የእምነት መግለጫዎችን ፈጥረዋል። እነዚህ ቀደምት ፕሮቴስታንቶች በተገቢው ምክንያት ለተሾሙት የዘመኑ የሃይማኖት ምሁራን እንዲህ ያለ ከፍተኛ አክብሮት ነበራቸው። እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ ያስቀመጣቸውን ባለሥልጣናት

እንዲያከብሩ ቅዱሳን መጻሕፍት የክርስቶስ ተከታዮችን እንዳስተማሩ ያምኑ ነበር። ብዙ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ስለዚህ ጉዳይ ይናገራሉ። ለምሳሌ ፣ በቲቶ 2 1፣15 ፣ ጳውሎስ ቲቶን በእነዚህ ቃላት አስተምሯል -

> አንተ ግን ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን ተናገር።...ይህን በሙሉ ሥልጣን ተናገርና ምከር ገሥጽም፤ ማንም አይናቅህ። (ቲቶ 2:1, 15).

> *የተሐድሶው ልብ የሥልጣን ጥያቄ ነበር ምክንያቱም ሌሎች ነገሮች ሁሉ ፣ የምናምናቸው ነገሮች ሁሉ ፣ ሥልጣናችን ምን እንደሆነ ከመረጥነው የሚመነጩ ናቸው… አዲስ ኪዳን ክርስቶስ የማዕዘን ራስ ድንጋይ እንደሆነ፤ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ሐዋርያትና ነቢያት የቤተክርስቲያን መሠረት እንደሆኑ ይነግረናል፡፡ ነገር ግን ከዚያ በኋላ የወንጌላዊያን ፣ የፓስተሮች እና የመምህራን ሥልጣናት በቤተክርስቲያን መኖር ጀመረ፡፡ የቤተክርስቲያን ሥልጣናት ለእኛ በጣም አስፈላጊዎች ናቸው ፣ ምክንያቱም እነርሱ ጥበብ ይኖራቸዋል እና በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ለተገለጠው ለእግዚአብሔር እውነት ራሳቸውን እንዲገዙ የሚያግዙ ልምዶችን ያገኛሉ። ነገር ግን እነዚያ ሥልጣናት ሁል ጊዜ ለጌታ ለኢየሱስ መገዛት እና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ አጠራጣሪ ያልሆነ ሥልጣን ማረጋገጫ መስጠት አለባቸው፡፡*
>
> — ዶ/ር ሪቻርድ ኤል ፕራት ፣ ጁኒየር

ይህ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እና በቤተ ክህነት ባለሥልጣን መካከል ያለው ሚዛን በተሃድሶ አራማጆች ዘንድ በተደጋጋሚ በሚነሳው የድሮ መፈክር ውስጥ ሊጠቃለል ይችላል - "ተሐድሶ ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ትታደሳለች" ወይም ብዙውን ጊዜ በላቲን ሐረግ "semper reformanda" - "ሁልጊዜ መታደስ" ማለት ነው፡፡ እነዚህ መፈክሮች የሚያመለክቱት የተሐድሶው ቤተክርስቲያን፣ የቤተ ክህነት ሥልጣናት አስፈላጊ ቢሆኑም ፣ ሁል ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥጥር ሥር መሆን አለባቸው የሚለውን አሳብ ነው።

በመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክ እምነት እና ቀደምት ፕሮቴስታንቶች ወቅት በሥነ -መለኮት ውስጥ ስለ ሥልጣን ያለውን አመለካከት ከተመለከትን፣ የዚህን ትምህርት ሦስተኛ ርዕስ ማለትም ወቅታዊ ፕሮቴስታንትነትን ከግምት ውስጥ ለማስገባት ዝግጁ ነን፡፡

## ወቅታዊ ፕሮቴስታንትዝም

"ሥልጣን" ዛሬ በብዙ የዓለም ክፍሎች በወንጌላውያን ፕሮቴስታንቶች መካከል ጠንካራ አሉታዊ ምላሾችን የሚያስነሳ አስተሳሰብ ነው። ብዙዎቻችን ሥልጣናት ብዙውን ጊዜ ኃይላቸውን እንዴት እንደሚጠቀሙበት እናያለን እና በተፈጥሮ እንቃወማቸዋለን። ቀደም ሲል እንዳየነው፣ በሺዎች ዓመታት ክርስቲያኖች በሥነ-መለኮት ውስጥ ከእነዚህ ጉዳዮች ጋር ታግለዋል። ስለዚህ ቅድመ አያቶቻችን ከሥነ -መለኮት ሥልጣንን ካስተናገዱበት መንገዶች ምን እንማራለን? ዛሬ ሥነ -መለኮትን ስንገነባ ለዘመኑ ወንጌላውያን የሥልጣን እሴቶች እና አደጋዎች ምንድናቸው?

ለቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ሊኖረን የሚገባውን የአመለካከት ዓይነቶች በማስተናገድ ስለ ወቅታዊ ፕሮቴስታንት እምነት ለመመለስ እንሞክራለን፡፡ ሁለተኛ በቤተክርስቲያን ስልጣን ላይ ሊኖረን የሚገቡ አንዳንድ አስፈላጊ አመለካከቶችን እንጠቁማለን። አስቀድመን ስለቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን እንመልከት፡፡

### የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን

*መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቲያኑ ላይ ያለው ሥልጣን በሁሉም የሕይወታቸው ክፍል ፍጹም ሥልጣን ነው። ይህን አለማድረግ በእውነት እራሳችንን እንደ እግዚአብሔር መቁጠር ነው። መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ፡ "እኔ ያንን ክፍል አልከተልም ግን ይህንን ክፍል እከተላለሁ" ወይም "ይህንን ትንሽ ጥቅስ እንጂ ያንን ትንሽ ጥቅስ አልታዘዝም" ማለት በአንድ መልኩ ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ እኛ ሥልጣን እንዳለን ማሰብ እና እውነት*

> *የሆነውን እና ያልሆነውን ፣ የምንከተለውን እና የማንከተለውን ለመወሰን መነሳት እና ያንን ስናደርግ እኛ እራሳችን ትናንሽ አማልክት ማድረግ ነው። እኛ ራሳችን የአጽናፈ ዓለሙ አምላክ አድርገናል። ያ ደግሞ ጣዖት አምልኮ ነው። ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍትን መካድ እና በሥልጣኑ በአንድ መንገድ አለመኖር እግዚአብሔርን ለመተካት እና ያንን ስልጣን ለራሳችን ለማድረግ መሞከር ነው። ስለዚህ በእውነቱ ለእግዚአብሔር ተገቢውን ቦታ እንደ የመጨረሻው ስልጣን እንዲሰጡ ቅዱሳት መጻሕፍት በሁሉም አካባቢ ወይም በሁሉም አካባቢዎች ማለት ይቻላል የክርስትያንን ሕይወት መምራታቸው በጣም አስፈላጊ ነው።*
>
> — ዶ/ር ማይክል ጄ ክሩገር

በዚህ ትምህርት ውስጥ እኛን የሚመለከቱን ሦስት ጉዳዮችን በመዳሰስ የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ወቅታዊ አመለካከቶችን እንመረምራለን፡፡ እነርሱም የቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጻፍ፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም እና የቅዱሳት መጻሕፍት ግልፅነት ናቸው። በዘመናችን በእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በርከት ያሉ የተለያዩ አመለካከቶች የተሐድሶ ባሕልን እንደከሚከተሉ ይናገራሉ፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጻፉ ላይ ዘመናዊ እይታዎች በመነሳት እነዚህን ዕይታዎች እንመለከታለን እና ዋጋቸውን እንገመግማለን።

## ቅዱሳት መጻሐፍት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጻፉ

በዘመናዊ ፕሮቴስታንቶች መካከል ቢያንስ ሦስት ቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መጻፉን በተመለከት ሦስት እይታዎች ታዋቂ ናቸው። በአንደኛው ጫፍ ላይ ብዙውን ጊዜ የፍቅር መነሳሳት ብለን የምንጠራው እይታ አለ። በሌላኛው ጫፍ ላይ በተመሳሳይ መልኩ ሜካኒካዊ መነሳሳት የሚባል እጅግ በጣም ከፍተኛ እይታ አለ። እናም በእነዚህ ጽንፍ ዕይታዎች መካከል ኦርጋኒክ መነሳሳት ተብሎ የሚጠራ አመለካከት አለ። የእነዚህን ሦስቱን እይታዎች በአጭሩ እንመልከት።

ሮማንቲክ መነሳሳት በበለጠ ሊበራል በሆኑ ፕሮቴስታንቶች በሰፊው ይደገፋል፡፡ በዚህ እይታ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ታላላቅ ጸሐፊዎች ፣ አርቲስቶች እና አቀናባሪዎች - እንደ ሼክርስፕር፣ ሬምብራንድ ወይም ባች - በኃይለኛ ተመስጦ ውስጥ ገብተዋል የሚል ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችን አነሳሳ፣ ግን እርሱ ጽሑፎቻቸውን በበላይነት አልተቆጣጠረም። በዚህ እይታ ቅዱሳት መጻሕፍት የሰዎች አስተያየት ብቻ ናቸው። ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት የማይሳሳቱ እና በቤተ ክርስቲያን ላይ ፍጹም ሥልጣን የላቸውም። አሁን ፣ ይህ ለመነሳሳት ያለ አመለካከት በተሐድሶ መንፈስ በሚጸኑ ሰዎች ውድቅ መሆን አለበት። ይህ አመለካከት የመጽሐፍ ቅዱስን ተዓማኒነት እና የመጨረሻውን ሥልጣን በመካድ ለሶላ ስክሪፕቱራ ማዕከላዊውን የፕሮቴስታንት ቁርጠኝነት ችላ ይላል፡፡



በፍቅር ተነሳሽነት ፣ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችን አነሳሳ ፣ ግን ጽሑፎቻቸውን በበላይነት አልተቆጣጠረም።

በሌላኛው ጫፍ ላይ ሜካኒካዊ መነሳሳት አለ ወይም አንዳንድ ጊዜ "የአምባገነንነት ተነሳሽነት" ተብሎ ይጠራል። በአንድ ወይም በሌላ ደረጃ ፣ ይህ አመለካከት የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲጽፉ በአንፃራዊነት ተቀባዮች ብቻ እንደነበሩ ያረጋግጣል። በዚህ አመለካከት ፣ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ራሱ የጻፈው ፣ ሰብዓዊ ጸሐፊዎች እንደ ታዛዥ

ጸሐፊዎቹ ሆነው ሲሠሩ ነበር። በአጠቃላይ ፣ ይህ አመለካከት የሰውን ጸሐፊ ታሪካዊ ዐውደ - ጽሑፍ እና የመጀመሪያውን ትርጉምን አስፈላጊነት በመካድ ከሶላ ስክሪፕቱራ ተሐድሶ መርህ ይርቃል። የተሐድሶ አራማጆች በጥንቃቄ ተመልክተውታል፤ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቀጥተኛ ትርጉም ዋጋ መካድ የቅዱሳት መጻሕፍትን ተግባራዊ ሥልጣን ያደናቅፋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ከእንግዲህ ሊገመገም እና ሊንከተል አይቻልም፣ እናም የራሳችንን ሀሳቦች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ እንገደዳለን። በውጤቱም ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ በሥነ-መለኮት ውስጥ እንደ ከፍተኛ ባለሥልጣናችን ሆኖ አያገለግልም፡፡



በሜካኒካዊ አነሳሽነት ፣ መጽሐፍ ቅዱስን የጻፈው እግዚአብሔር ሲሆን የሰው ጸሐፊዎች ዘጋቢዎች ሆነው እንዳገለግሉ ይናገራል፡፡

የዘመናዊው የፕሮቴስታንት ሥነ-መለኮት መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተጻፈ ለሚለው ኦርጋኒክ የሚለውን እይታ እንደገና በማረጋገጥ ከሁለቱም የፍቅር እና የሜካኒካዊ ተነሳሽነት ጽንፍ መራቅ አለበት። በኦርጋኒክ እይታ፣ እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲያን ጽሑፎቻቸውን እንዲጽፉ አነሳሳቸው እንዲሁም ሳይሳሳቱ በሥልጣን እንዲጽፉ መራቸው፡፡ ግን እሱ የግል ሀሳቦቻቸውን፣ ተነሳሽነቶቻቸውን፣ ስሜቶቻቸውን ወይም ሥነ-መለኮታቸውን አላስወገደም። መለኮታዊና ሰብዓዊ ገጽታዎች አልተቃረኑም፡፡ ይልቁንም ሁሉም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጊዜ የማይሽራቸው እውነቶች ያቀርባል ፣ ነገር ግን በሰዎች፣ በባህላዊ ዐውዶች ውስጥ የቀረቡ ናቸው፡፡ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ለሁሉም ጊዜያት ተገበ ናቸው፣ ግን ትምህርቶቹ ከተለዩ ሁኔታዎች አውድ ጋር የተሳሰሩ ናቸው። የኦርጋኒክ እይታ የፕሮቴስታንት አመለካከት የሰውንም ሆነ የመለኮትን፣ የታሪካዊውን እና የመላውን መጽሐፍ ቅዱስ ባሕርያትን ያጎላል። በዚህ እይታ፣ የሶላ ስክሪፕቱራ ዶክትሪን ተጠብቆ ይቆያል። ያለምንም ጥርጥር ፕሮቴስታንቶች መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተጻፈ ለሚለው ካሉ ሦስት ዋና ዋና መንገዶች ፣ የኦርጋኒክ እይታ ትምህርት የፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶን አመጣጥ እና መሪ መርሆዎች ጋር በጣም የሚስማማ ነው።



በኦርጋኒክ እይተ፣ እግዚአብሔር የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፊዎችን በበላይነት ይመራቸው ነበር፤ ነገር ግን የግል አሳቦቻቸውን፣ መነሳሳታቸውን፣ ስሜቶቻቸውን ወይም ሥነመለኮታቸውን አላስወገደም፡፡

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ከምወዳቸው ነገሮች አንዱ የደራሲዎቹ የተለያዩ እና መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዳቸው ደራሲያን አማካይነት ማን እንደነበሩ ፣ ልምዶቻቸው ፣ ህይወታቸውን ተጠቅሞ እግዚአብሔር ማን ነው እና ለእኛ ምን ማለት እንደሆነ ሙሉ ምስልን ለማምጣት እንዴት እንደሰራ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የተለያዩ ጸሐፊዎችን እንዴት እንደተጠቀመ ስናይ ፣ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው እየሠራ የሚጽፉትን፣ የሚናገሩትን፣ ግን በራሳቸው ስብዕና እና በራሳቸው ልምዶች አማካይነት የሰጣቸው ይመስላል፡፡ ስለዚህ

*ሕያው ነው ፣ ጥልቅና ሙሉ ነው፡፡ ሜካኒካዊ አልነረበም፤ ብዙ ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ከእርሱ ጋር እንዲገናኙ አስችሏቸዋል። እግዚአብሔር እኛ የምናሳልፋቸውን ልምዶች ያደንቃል ብዬ አስባለሁ፣ እናም መንፈስ ቅዱስ በእነዚያ ጸሐፊዎች ውስጥ በማደር የሚጽፉትን መልዕክት ሰጣቸው እና በሰብዕናቸውም ውስጥ ሥራውን ሠራ፡፡*

*— ዶ/ር ዳን ላቺች*

*የዘመናችን የፕሮቴስታንት የሥነ-መለኮት ሊቃውንት የመነሳሳትን ኦርጋኒክ ተፈጥሮ ከማጉላት በተጨማሪ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም በትክክል በመገምገም የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን መገምገም አለባቸው።*

## ትርጉም

*አሁንም በቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ላይ የፕሮቴስታንት አስተሳሰብን የሚወክሉ የተለያዩ አቋሞች አሉን። ግን ሁሉም አማራጮች የተሃድሶውን ፅንሰ -ሀሳብ አያራምዱም። በአንደኛው ጫፍ ላይ "የዘመናዊ ብዝሃነት" ብለን የምንጠራው እይታ አለ። በሌላኛው ጫፍ ላይ "ቀለል ያለ ልዩነት" ብለን የምንጠራው እይታ አለ። እና በመሃል ላይ "ውስብስብ ልዩ" ብለን የምንጠራው እይታ አለ። በመጀመሪያ ዘመናዊው የብዙነት የሚለውን እንመልከት፡፡*

*ከቅርብ አሥርተ ዓመታት ወዲህ አንዳንድ የፕሮቴስታንት የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍት የተለያዩ ትርጉሞች እንዳሏቸው ስለሚያምኑ ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፎች ብዙነት ይናገራሉ። ነገር ግን ክላሲካል ብዝሃነት በመጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ አመጣጥ ምክንያት በርካታ ትርጉሞችን ያረጋገጠ ቢሆንም ፣ የዘመናችን ብዝሃነት ብዙውን ጊዜ አሻሚ በሆኑ የሰው ቋንቋ ዎች ላይ የተመሠረተ ነው።*

*በተግባር ሲተይ የዘመናችን ብዝሃነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባቦች ለተርጓሚዎች ባዶ ዕቃዎች መሆናቸውን ያስተምራል። አሁን ይህንን አመለካከት የሚጠብቁ ሰዎች፣ አንድ ዕቃ የተሰጠው ቅርፅ እንዳለው ሁሉ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ሰዋሰው አንዳንድ መሠረታዊ የትርጓሜ መለኪያዎችን እንደሚያዘጋጁ ይገነዘባሉ። ነገር ግን በእነዚህ መለኪያዎች ውስጥ ልዩ ትርጉሙ በመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ይሰጣል። በዚህ መሠረት ተሃድሶው በሴንሱስ ሊትራስ ላይ የሚያደርገውን ትኩረት መቃወም አለብን ብለን ተከራክሯል። ይልቁንም ፣ ለጽሑፉ የመጀመሪያ ወይም ቀጥተኛ ትርጉም ብዙም ወይም ምንም ሳንጨነቅ የራሳችንን ትርጓሜዎች ወደ ምንባቦች ማፍሰስ አለብን።*

*እንደ አለመታደል ሆኖ ይህ የወቅቱ የብዙነት አስተሳሰብ የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን ባዶ ያደርገዋል። ለሰው ተርጓሚዎች የራሳቸውን ሐሳብ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የማፍሰስ መብት ይሰጣቸዋል። እናም በዚህ ምክንያት እኛ ልንቀበለው አይገባም።*

*በሌላኛው ጫፍ ላይ "ቀለል ያለ ልዩነት" ጽንሰ -ሀሳብ አለ። ይህ አመለካከት እያንዳንዱ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች አንድ ትርጉም ብቻ አላቸው የሚለውን አስተሳሰብ ያበረታታል። ግን አንድ ነጠላ ትርጉም ውስብስብ ሊሆን እንደሚችል አይቀበልም። ለምሳሌ ዮሐንስ 3:16 ን እንውሰድ።*

> በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። (ዮሐንስ 3:16).

*ቀለል ያለ ልዩነትን በአእምሮው የያዘ አንድ ክርስቲያን እንደዚህ ያለ ነገር ሊናገር ይችላል - "ይህ ጥቅስ በጣም ቀላል ነው። ዮሐንስ 3:16 በክርስቶስ ማመን እንዳለብን ይነግረናል።"*

*ዮሐንስ 3:16 ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ በጣም ቀላል በሆነ መንገድ የሚያጠቃልሉት የታወቀ ጥቅስ ነው። ግን በእውነቱ ይህ ጥቅስ ሁሉንም ዓይነት በጣም ሰፊ ርዕሶችን ይነካል። ስለ እግዚአብሔር ፍቅር በግልፅ ይናገራል። የክርስቶስን ትስጉት ፣ ሞትና ትንሣኤ ያስታውሰናል። ስለ ዓለም፣ ስለ ዘላለማዊ ቅጣት እና ስለ ዘላለማዊ ሕይወት ይናገራል። እያንዳንዳቸው እነዚህ ርዕሶች በራሱ የተወሳሰቡ ናቸው እና በመካከላቸው እጅግ በጣም ብዙ ምክንያታዊ ግንኙነቶች አሉ። ስለዚህ ዮሐንስ 3:16 አንድ ፣ አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም አለው ማለታችን ትክክል ቢሆንም ፣ የዚህ ትርጉም ውስብስብነት እኛ ከቻልነው ከማንኛውም ማጠቃለያ ይበልጣል። እና የተለያዩ አስተርጓሚዎች የአንድ ትርጉሙን የተለያዩ ገጽታዎች በትክክል ማጉላት ይችላሉ።*

*የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በጣም የተወሳሰበ ከመሆኑ የተነሳ ሁል ጊዜ ከትርጓሜዎቻችን የሚበልጥ መሆኑን ማየት ሳንችል ፣ ከባድ አደጋ እንጋፈጣለን። የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጓሜ ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በቅርበት ለመለየት አደጋ ላይ*

ነን። የእኛ ትርጓሜ የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን ይወስዳል ፣ እናም እኛ ሶላ ስክሪፕተራን እንቀበላለን - መጽሐፍ ቅዱስ ሁል ጊዜ ከትርጓሜዎቻችን በላይ ይቆማል የሚለውን እምነት።

በእይታዎቹ መሃል ላይ "የተወሳሰበ ልዩነት" አለ፣ እሱም ከመጀመሪያዎቹ የተሃድሶ እይታዎች ጋር የሚስማማ ነው። የዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫ በምዕራፍ 1 ፣ ክፍል 9 ላይ እነዚህን ቃላት በሚናገርበት ውስብስብ ልዩነትን ይገልጻል።

> ስለማንኛውም የቅዱሳት መጻሕፍት እውነተኛ እና ሙሉ ስሜት (ብዙ ሳይሆን አንድ ነው) ጥያቄ ሲኖር ፣ የበለጠ በግልጽ በሚናገሩ ሌሎች ቦታዎች መፈለግ እና መታወቅ አለበት።

በዚህ እይታ ፣ እያንዳንዱ ምንባብ አንድ ትርጉም አለው። ግን ይህ አንድ ትርጉም ውስብስብ እና ዘርፈ ብዙ ነው፣ በጠቅላላው የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት በተቋቋሙት በብዙ ተደጋጋሚነት ድር ተገለጠ።

> *ሰዎች በተለያዩ መንገዶች እንደ "ልዩነት" የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ። ነገር ግን በጥሩ ሁኔታ ፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ልዩነት አንድ እሴት አለው ፣ እያንዳንዱ ክፍል አንድ የተዋሃደ ትርጉም አለው ማለት ነው። አሁን ያ ትርጉም ያለው አንድነት ውስብስብ ነው። ውስብስብ ነው። ቀላል አይደለም። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሳሰበ ስለሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቡን አንድ ትርጉም በአንድ ሐረግ ወይም በጣም ቀላል በሆነ ዓረፍተ ነገር ማጠቃለል እንደቻልን አይደለም። ነገር ግን እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድ ነው። ይህ ማለት አንድ ያልተለመደ ነው ማለታችን ነው - አንድ ላይ ያያይዛል። ከአንድነት ልዩነት ተቃራኒ የሆነው ብዝሃነት ፣ ይህ መጽሐፍ በእርግጥ ያለው ምን እንደሆነ ፣ ይህ ምንባብ ምን ማለት እንደሆነ እና ያ ምንባብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና ወደፊት እና ወደ ላይ መሄድ እንዲችሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ማንኛውም ምንባብ ብዙ ትርጉሞች አሉት ብሎ ያስባል። እነዚህ የተለያዩ እሴቶች ወይም የዚያ ምንባብ ትርጉሞች ምንም ዓይነት ትስስር ቢኖራቸው ምንም አይደለም። እውነታው ግን ልዩነቱ እንደ ወንጌላዊያን የምናምነው ነው ፣ ግን ቀለል ያለ ልዩነት አይደለም። እሱ ውስብስብ ልዩነት ነው። ስለዚህ ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ፣ እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ማንኛውም ምንባብ ፣ አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም እንዳለው እናውቃለን ፣ እናም በዚህ ሁኔታ ፣ እሱ ልዩ ያልሆነ ነው።*
>
> *— ዶ/ር ሪቻርድ ኤል ፕራት ፣ ጁኒየር*

የተወሳሰበ ልዩ ልዩነት የተሐድሶ አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱስ እኛ እስክናቀርብ ድረስ ሥልጣን ያለው ትርጉም እንደሚሰጥ ያረጋግጣል። እንዲሁም ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ቀላል የመጽሐፍ ቅዱስ ማጠቃለያዎቻችን ደረጃ ዝቅ ከማድረግ ይከለክለናል። እያንዳንዱ የቅዱሳት መጻሕፍት ጽሑፍ ጽሑፉን ለመተርጎም ከምናደርገው ከፍተኛ ጥረት በላይ እንደ ሥልጣን ይቆማል። ይህ የተወሳሰበ የልዩነት አመለካከት በዘመናችን የተሐድሶን ሥነ -መለኮት የበለጠ ለማሳደግ የሚያስችለንን የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም የምንይዝበትን መንገድ ያቀርባል።

በቅዱሳት መጻሕፍት በመንፈስ ቀዱስ መሪነት መጻፍ እና ትርጉም ላይ ወቅታዊ የፕሮቴስታንት አመለካከቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን ተመልክተናል። አሁን ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ግልፅነት ከዘመናዊ የፕሮቴስታንት አመለካከቶች አንጻር እንመለከታለን፡፡

## ግልጽነት

ከሶስት ነጥቦች አንፃር በአንድ ነጥብ ላይ ለማሰብ እንደገና ይረዳናል። በአንደኛው ጫፍ ወደ ድብቅነት ከሚወስደው ወቅታዊ ዝንባሌዎች ጋር እንጋፈጣለን። በሌላ በኩል ፍጹም ግልፅነትን የሚያራምዱ ወቅታዊ ዝንባሌዎች ያጋጥሙናል። ነገር ግን በመሃል ላይ የግልጽነት ደረጃዎቻችን የሚያራምደው የተሃድሶ ትምህርት አለ።

> *ቅዱሳት መጻሕፍት የግልጽነት ባሕሪ አለው፡፡ አሁን ያ ማለት ሁልጊዜ ለእኛ ለመረዳት ቀላል ነው ማለት አይደለም፡፡ በእርግጥ ጴጥሮስ ጳውሎስ የጻፋቸው አንዳንድ ነገሮች ለመረዳት አዳጋች እንደሆኑ ተናግሯል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ስንተረጉመው የችግር ምንጭ ምን እንደሆነ መረዳት እንዳለብን ያሳየናል፡፡ ከችግሮቹ አንዱ ውስን ፍጥረታት መሆናችን ነው።... ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ያለ ውስብስብ ወደሆነ ርዕስ ጉዳይ ስንመጣ ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እራሱ ግልፅ ቢሆንም ፣ አንዳንድ ጊዜ ለመረዳት ፈታኝ ነው። ግን በጣም አስፈላጊው የመጨረሻው ነገር - እና የዌስት ሚኒስተር መግለጫ ስለዚህ እንዲህ ይላል - ለመዳን አስፈላጊ*

*የሆኑት ነገሮች ቀላል ስለሆኑ ማንም ሰው እንኳን ሊረዳቸው ይችላል።*

*— ቀሲስ ሚካኤል ጄ ግሎዶ*

ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ ድብቅ ወይም ከኛ የተሰወረ አድርገው የሚመለከቱ ፕሮቴስታንቶችን ማግኘት አስቸጋሪ አይደለም። ብዙውን ጊዜ በዲኮንስትራክሽን መንፈስ እና በድህረ ዘመናዊ ትርጓሜዎች መንፈስ እነዚህ ፕሮቴስታንቶች ስለ ሌሎች ጽሑፎች ሁሉ በሚያስቡበት መንገድ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስባሉ። ልክ እንደሌሎች ጽሑፎች ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን የሚቃረን እና ራሱን የሚያጠፋ ነው ብለው ስለሚያምኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ደብዛዛ እንደሆኑ አድርገው ይቆጥሩታል። በእነርሱ እይታ ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ታሪክ በጣም ብዙ የሥነ-አፈታት ችግሮችን ገልጧል ፣ እናም ዛሬ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት መረዳት እንዳለብን ለመወሰን ፈጽሞ የማይቻል ነው።

በሌላ በኩል ፣ አንዳንድ የዘመኑ ፕሮቴስታንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም ግልፅነት ያምናሉ። በፍጥነት እና በቀላሉ ሊረዷቸው ስለሚችሉ ሁሉንም ቅዱሳት መጻሕፍት ማለት ይቻላል ግልፅ አድርገው ይመለከቱታል። ብዙውን ጊዜ እንደዚህ ያሉ አመለካከቶች አራማጆች በጣም ጠባብ ከሆኑት የራሳቸው የክርስቲያን ማህበረሰቦቻቸው የማይመጡትን ሁሉንም ትርጓሜዎች ለማስተናገድ ፈቃደኞች አይደሉም፡፡


የቅዱሳት መጻሕፍትን ግልፅነት ማጋነን ዛሬ በፕሮቴስታንት ወግ ውስጥ ለብዙ የሥነ-መለኮት ምሁራን ትልቅ ፈተና ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትን ከዘመናዊ ጥርጣሬ እና ተጠራጣሪነት እንዲርቅ አጥብቀን እንፈልጋለን። ነገር ግን የቅዱሳት መጻሕፍትን ግልፅነት በዚህ መንገድ ቀላል አድርገን ካቀረብን በቅዱሳት መጻሕፍት ግልፅነት ላይ የተሐድሶን አመለካከት ማስጠበቅ አንችልም። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ፣ ቀደምት ተሐድሶ አራማጆች አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለመረዳት ቢከብዱም መረዳት ግን እንደሚቻል ያምናሉ፡፡

በቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽነት ላይ ባለው የአመለካከት መስመር ላይ የግልጽነት ደረጃዎችን የሚቀበል አቋም አለ። ይህ በዌስት ሚኒስተር የእምነት መግለጫ ምዕራፍ 1 ፣ ክፍል 7 የተቀበለው አቋም ነው።

> *በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያሉት ነገሮች ሁሉ ለራሳቸው ግልጽ አይደሉም ወይም ለሁሉም ግልፅ አይደሉም ፣ ነገር ግን ሊታወቁ ፣ ሊታመኑ እና ለድነት ሊጠበቁ የሚገባቸው ነገሮች በግልጽ ተተርጉመው በመጽሐፍ ቅዱስ ወይም በሌላ ቦታ ክፍት የሆኑ፣ የተማሩት ብቻ ሳይሆን ያልተማሩት፣ በተለመዱ ዘዴዎች በተገቢው መንገድ በቂ ግንዛቤ ሊያገኙ ይችላሉ።*

ልብ በሉ ፣ መግለጫው "ለድነት አስስፈላጊ …" የሚለውን በአንድ ወይም በሌላ ቦታ በግልጽ እንደሚለይ ልብ በሉ። ግን ደግሞ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያሉት ሁሉም ነገሮች እኩል ግልፅ እንዳልሆኑ ይቀበላል። በሌላ አነጋገር መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ ግልጽ አይደለም ወይም ሙሉ በሙሉ ደብቅ አይደለም።

በቀደመው ትምህርት በተለያዩ የክርስትና ትምህርቶች ውስጥ ባለን በተለያዩ የመተማመን ደረጃዎች መካከል እንደ ተለየን አስታውሱ። እኛ ‹የእርግጠኝነት ኮኔ› ብለን የጠራነውን ሞዴል ተጠቀምን። የእኛን የእርግጠኛነት ታችኛው ክፍል ፣ እኛ ስለእነርሱ ዝቅተኛ የመተማመን ደረጃ ስላለን አጥብቀን የምንይዛቸው እምነቶች አሉን። ከላይ እኛ አጥብቀን የምንይዛቸው እነዚያ ዋና እምነቶች አሉን ፣ እነርሱን መተው የክርስትናን እምነት መተው ነው። እናም በእነዚህ ጽንፎች መካከል እኛ የምናምንባቸው ሌሎች ነገሮች ሁሉ በተለያዩ የመተማመን ደረጃዎች ላይ ይገኛሉ፡፡




የእርግጠኝነት ኮኔ የመተማመንን መጠን እንድናይ ይረዳናል፣ የተለያዩ እምነታችንን የምንይዝበት መንገዶች።

በብዙ መልኩ ፣ የቅዱሳት መጻሕፍትን ግልፅነት በተመሳሳይ ሁኔታ ለማሰብ ይረዳል። በመጀመሪያ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ገጽታዎች-ለመዳን የሚያስፈልገውን እውቀት ጨምሮ-ለመረዳት ትንሽ ወይም ምንም የምሁራዊ ጥረት አያስፈልጋቸውም። የዌስት ሚኒስተር መግለጫ እንዳስቀመጠው፣ “የተማሩት” እና “ያልተማሩ” ሰዎች እነዚህን ነገሮች ሊረዱት ይችላሉ። ሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎችም ከዚህ ምድብ ጋር ይጣጣማሉ። በእርግጥ እጅግ በጣም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በቀላሉ ለመረዳት ቀላል ናቸው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ ወይም አብርሃም፣ ሙሴ እና ዳዊት የተባሉ ሰዎች እንደነበሩ ወይም እስራኤል ወደ ግብፅ እንደገባች እና በኋላም በግዞት እንደገቡ ማየት ከባድ አይደለም። አዲስ ኪዳን ኢየሱስ በናዝሬት እንዳደገ እና ሐዋርያትም እንደነበሩ በግልፅ ያስተምራል። እነዚህ እና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ባህሪዎች በጣም ግልፅ ስለሆኑ ማንም እነሱን ለማወቅ ምሁራዊ ወይም ትምህርታዊ ጥረት ማድረግ አያስፈልገውም።

> በጣም መሠረታዊ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ለመረዳት ልዩ ዘዴዎች ያስፈልጉናልን? መልሱ “አይደለም” ነው ብዬ አምናለሁ ምክንያቱም አብዛኛው መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ግልፅ ነው… ጴጥሮስ እንደሚነግረን ፣ እግዚአብሔር ኃይሉንና ማንነቱን እንዲሁም ለሕይወት፣ እግዚአብሔርን መስሎ ለመኖር እና ለድነት የሚሆነውን ሁሉ ገልጦልናል ፣ ምክንያቱም በቸርነቱ ጠርቶናል። ወይም የዌስት ሚኒስተር የእምነት መግለጫ ምዕራፍ 1፣ ክፍል 6 እንዳስቀመጠው ፣ “ለራሱ ክብር ፣ ለሰው ልጅ መዳን ፣ ለእምነት እና ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ በተመለከተ የእግዚአብሔር ምክር በሙሉ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በግልጽ ተቀምጧል ወይም በመልካም እና አስፈላጊ ውጤት ያላቸውን ከቅዱሳት መጻሕፍት ማውጣት ይቻላል፡፡» ስለዚህ ፣ ማንኛውም መደበኛ ሰው ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሁር ባይሆኑም ፣ በተለያዩ ተገቢ ዘዴዎች እና እግዚአብሔር በሰጠን መሠረታዊ እውቀት አማካኝነት መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት ይችላል... አንድ ሰው የገረመው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለመረዳት አዳጋች መሆኑን ሳይሆን በተለይ ግልፅ ክፍሎች እውነትን እና መዳንን የሚያውጁ ማንም ሊረዳቸው የሚችሉ ክፍሎች እንደሆኑ ተናግሮ ነበር። እነዚህ ነገሮች ያስደነግጣሉ፡፡ ስለዚህ ስለ መዳን፣ ስለ ሰው ኃጢአተኛነት፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ የሚያቀርበውን ድነት እና ስለ መጪው ፍርድ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንድ ሰው ማንበብ እስከቻለ ወይም ሌላ ሰው ሲያነብ እስከሚሰማ ድረስ መልካም ነው፡፡
>
> — ዶ/ ቢአሲ ቼን ፣ ትርጉም ነው

በሁለተኛ ደረጃ አንዳንድ የቅዱሳት መጻሕፍት ገጽታዎች የሚታወቁት እንደ ጥንታዊ ታሪክ፣ የጽሑፍ ትችት ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቋንቋዎች፣ የትርጓሜ ዘዴዎች ወይም ሥነ -መለኮት ያሉ ትምህርቶችን በሚያጠኑ ተማሪዎች ብቻ ነው። ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል እንደ ጳውሎስ የቃላት ፍቺ ወይም የዘፍጥረት መጽሐፍ ታሪካዊ ዓላማ ያሉ ነገሮችን ልንቆጥር እንችላለን።

እነዚህ እና ሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ገጽታዎች የበለጠ ምሁራዊ ትኩረት ይፈልጋሉ። ነገር ግን በቂ በሆነ የአካዳሚክ ጥረቶች መጀመሪያ ላይ ግልጽ ያልሆኑ የሚመስሉ ብዙ ነገሮች ለእኛ የበለጠ ግልጽ ይሆናሉ።

በመጨረሻ ፣ አንዳንድ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች የቱንም ያህል ጥረት ብናደርግ ግልፅ ያልሆኑ ይመስላሉ። ከእነዚህ የቅዱሳት መጻሕፍት ገጽታዎች የበለጠ ግልፅ ምሳሌዎች የሚነሱት እንደ ሳሙኤል፣ ነገሥታት እና ዜና መዋዕል ወይም የአዲስ ኪዳን ወንጌሎች ያሉ ትይዩ የሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎችን ለማስማማት ስንሞክር ነው። በእነዚህ አካባቢዎች ትልቅ እመርታ ቢታይም አሁንም ብዙ ችግሮች ሊፈቱ የማይችሉ ይመስላሉ።

ስለዚህ ፣ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ስንቀርብ፣ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጽታዎች ከሌሎቹ የበለጠ ግልፅ መሆናቸውን ሁል ጊዜ ማስታወስ አለብን። ይህንን እውነታ ስንጋፈጥ ብቻ ነው የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን በኃላፊነት መያዝ የምንችለው። እያንዳንዱ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ያለ ጥርጥር ሥልጣን ያለው መሆኑ እውነት ነው። ነገር ግን በተግባራዊ ደረጃ ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት የተለያዩ ክፍሎች አንጻራዊ ግልፅነት ላይ በመመስረት፣ የእርሱን ሥልጣናዊ መመሪያ ወደ ተለያዩ ደረጃዎች ልንረዳውና ልንጠቀምበት እንችላለን። ስለዚህ በዘመናችን የተሐድሶን ወግ ለመጠበቅ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ግልጽነት ላይ ከዘመናዊ ጽንፎች መራቅ እና ግልጽነት የደረጃ ጉዳይ መሆኑን ማረጋገጥ አለብን።

በእነዚህ የዘመኑ የፕሮቴስታንት አመለካከቶች በቅዱሳት መጻሕፍት ስልጣን ላይ በአእምሯችን ይዘን ፣ በዛሬው ሥነ-መለኮት ውስጥ ትኩረታችንን ወደ ቤተክርስቲያን ሥልጣን ማዞር አለብን።

## የቤተክርስቲያን ሥልጣን

እኛ በሁለት አቅጣጫዎች ላይ እንደገና እናተኩራለን -በመጀመሪያ የዘመኑ የፕሮቴስታንት ሥነ-መለኮት ምሁራን ያለፉትን የቤተ -ክርስቲያን ባለሥልጣናትን እንዴት ማየት እንዳለባቸው እንመለከታለን። ሁለተኛ  የዘመኑ የፕሮቴስታንት ባለሥልጣናትን እንዴት ማየት እንዳለባቸው እንነጋገራለን። በመጀመሪያ ስለቀደመችው ቤተክርስቲያን ሥልጣን ያላቸውን አመለካከት እንመልከት፡፡

### የቀድሞ ባለሥልጣናት

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ቀደምት ፕሮቴስታንቶች መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያናቸው ብዙ እውነቶች እንዳስተማረ ተረድተው ነበር። በዚህም ምክንያት ለቀደሙት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ትምህርቶች፣ የሃይማኖት መግለጫዎች እና ለረጅም ጊዜ የቤተክርስቲያን ወጎች ተገቢውን አክብሮት ለመስጠት ፈልገው ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ የጥንት ፕሮቴስታንቶች የቤተክርስቲያኒቱን ትምህርት እንደ ጊዜያዊ ፍርድ ተቀብለዋል። ሆኖም እነርሱም ይህንን ልምምድ በቤተክርስቲያን አስተምህሮዎች ላይ የቅዱሳት መጻሕፍትን የበላይነት በጠንካራ ማረጋገጫ አረጋግጠዋል። እነርሱ ቀደም ባሉት ላይ ተመርኩዘው ገንብተዋል ፣ ነገር ግን የቤተክርስቲያናኒን ትምህርቶች ሁሉ ለማያጠራጥር የቅዱስ ቃሉ መመዘኛ እንዲፈተሹ አድርገዋል፡፡

እንደ አለመታደል ሆኖ ዛሬ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት የዚህን ቀደምት የፕሮቴስታንት አቋም በሁለቱም በኩል አጥብቀው ለመያዝ ይቸገራሉ። አንዳንዶች ወደ ባህላዊነት በጣም ዘንበል ይላሉ። ሌሎች ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ይዘራሉ። ነገር ግን በፕሮቴስታንት ወግ ውስጥ ብዙዎች በእነዚህ ጽንፎች መካከል ሴሜፐር ሪፎርማንዳ ይለማመዳሉ።

በአንድ በኩል አንዳንድ የዘመኑ ሥነ-መለኮት ምሁራን “ወግ አጥባቂ” ወጥመድ ውስጥ ይወድቃሉ። በባህላዊነት፣ እኛ በመካከለኛው ዘመን የሮማን ካቶሊክ ባህላዊነት ወደሚመስሉ ልምምዶች ያዘነብላሉ ማለታችን ነው። አሁን የፕሮቴስታንት የሥነ-መለኮት ሊቃውንት የቅዱሳት መጻሕፍትን ሥልጣን ያረጋግጣሉ እና በእርግጥ የካቶሊክን ወጎች ውድቅ ያደርጋሉ። ግን ብዙ ጊዜ ወግ አጥባቂዎች ያለፉትን የእምነታቸውን መግለጫዎች በጣም ከፍ አድርገው ይመለከታሉ፣ በተግባራዊ ደረጃ ፣ ያለፈውን በበቂ ሁኔታ መመርመር አቅቷቸዋል።

> *እኛ ፕሮቴስታንቶች ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የሚስማማውን የማግስተሪየም ወይም የቤተክርስቲያን ወግ ሀሳብ እንቃወማለን፡፡ አሁንም በተግባር አንዳንድ ጊዜ እንዲሁ እናደርጋለን። ቤልጂክ ወይም ሄይድበርግ ወይም ለብዙዎቻችን  የዌስት ሚኒስተር የእምነት መግለጫ የሚያነሉ ሰዎችን ምናልባት ያውቁ ይሆናል። በእርግጥ ለብዙዎቻችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አንድ ዓይነት ስልጣን አግኝቷል፡፡ ያም ሆኖ ልክ በዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫ የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍት በሁሉም የቤተ*

*ክርስቲያን ጉባኤዎች፣ በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ሥነ -መለኮታዊ ክርክሮች ላይ የመጨረሻው ሥልጣን ነው ይላል … ወግ ጥሩ መመሪያ ነው ፣ ግን አስፈሪ ጌታ ነው። እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር ተልእኮ ውስጥ የምንጫወተው ሚና አለን፣ እናም የቅዱሳት መጻሕፍትን ታሪክ ከሌላው ምሳሌ፣ ከባሕል ምሳሌ እንጠቀማለን፤ ነገር ግን በእነዚህ ነገሮች አንገዛም፡፡*

*— ዶ/ር ግሪጎሪ አር*

በሌላ በኩል አንዳንድ ዘመናዊ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ከቀደምት የቤተ ክህነት ሥልጣን ጋር ሲገናኙ ወደ ተቃራኒው ጽንፍ ይሄዳሉ። በክርስቲያናዊው የአብርሆት ዘመናዊነት ውስጥ “መጽሐፍ ቅዱሳዊነት” ሊባል በሚችለው ውስጥ ይወድቃሉ። እነዚህ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት እያንዳንዱ ሰው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መጥቶ እያንዳንዱን ሥነ-መለኮታዊ ጉዳይ ያለፈው የፕሮቴስታንት ወግ ሳይረዳ መወሰን አለበት የሚል እይታ አላቸው።

*ለዘመናት ሁሉ ለተሐድሶ አራማጆች እና ለክርስቲያኖች ፣ ቅዱሳት መጻህፍት የመለኮታዊ መገለጥ ምንጭ እና ምስክር መሆናቸውን ተረድተዋል። ግን ይህ ለክርስቲያኖች ወጎች አያስፈልገንም ወይም እኛ በተወሰነ ወግ ውስጥ መገኘት የለብንም ማለት አይደለም። ስለዚህ ይህ ሀሳብ ሶላ ስክሪፕቱራ መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበብ በስተቀር ሁሉንም የእምነት መግለጫዎች አለመቀበል የተሐድሶ አራማጆች መልዕክት አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ወደፊት ለመሄድም የጥበብ መንገድ አይደለም፡፡*

*— ዶ/ር ዮናታን ቲ ፔኒንግተን*

ደጋግመው የፕሮቴስታንት የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ባሕላዊውን አስተሳሰብ በመቃወም “ቤተክርስቲያን የምትናገረው ምንም ነገር ቢሆን እኔ የምጨነቀው መጽሐፍ ቅዱስ ለሚናገረው ነገር ብቻ ነው።” የሚል ምላሽ ይሰጡ ነበር፡፡ ይህ ዓይነቱ አነጋገር ቅዱሳት መጻሕፍት የመጨረሻው ሥልጣን ያለውን መሆኑን ከመግለጽ የዘለለ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ለቤተክርስቲያን የሰጠውን ጥበብ ችላ ይላል። ይልቁንም ሥነ-መለኮታዊ ፍርድ የሚሰጠው በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ላሉት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ብቻ ነው።

ዛሬ በተሃድሶ መንፈስ ለመቀጠል፣ የሰምፔር ሪፎርማን መርህ እንደገና ማረጋገጥ አለብን። የተሐድሶ ትውፊትን አስፈላጊነት ችላ ሳንል የቅዱሳት መጻሕፍትን የበላይነት ለማረጋገጥ መጣር አለብን።

የሰምፔር ሪፎርማን ዛሬ የጥንቶቹ የቤተክርስቲያን አባቶች እና ጉባኤዎች ብቻ ሳይሆኑ የራሳችንን መግለጫ እና ወጎች እንደ ጊዜያዊ ፍርድ መቀበልን ይጠይቃል። ነገር ግን እነዚህ ባለሥልጣናት ከጥንት ጀምሮ ሁል ጊዜ ለማይጠረጠር የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ተገዢ መሆን አለባቸው። ዛሬ ተሐድሶውን የበለጠ ለማስፋት በቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣን ሥር ካለፉት ጊዜያት ጀምሮ ለቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ይህን ዓይነቱን ክብደት እንዴት መስጠት እንደሚቻል መማር አለብን።

*የሰምፐር ሪፎርማንዳ ሀሳብ በእውነቱ የቤተክርስቲያኒቱ ተሃድሶ ሁል ጊዜ ተሃድሶ መሆኑን ያስተላልፋል። እና አስፈላጊ የሆነው ምክንያት ቤተክርስቲያን ሁል ጊዜ በቅዱስ ቃሉ ስልጣን ስር ትቆማለች የማስተላለፊያ መንገድ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ በማንኛውም ልምምዶቻችን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነው ነገር ውጭ እንደምንኖር ባወቅን ጊዜ ተሃድሶ ለማድረግ ፈቃደኞች መሆን እንዳለብን ያሳስበናል፡፡… እኛ በቅዱሳት መጻሕፍት ሥር እንኖራለን፤ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜዎቻችንን እንኳን ለመፈተሽ ፈቃደኛ መሆን አለብን። ግን በማንኛውም ጊዜ ወቅታዊ በሆነ በማንኛውም ነገር ብቻ መሄድ አንችልም። ቤተክርስቲያን ሁል ጊዜ በተሐድሶ ውስጥ እንድትሆን ከፈለግን ያለፈውን ነገር መመልከት ይኖርብናል፡፡ በተለያዩ ዘመናት የነበሩ ሰዎች ምን ሲያስቡ እንደነበር - የእግዚአብሔር መንፈስ እንዴት ይሠራ እንደነበር ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህም እኛ የምንናገረው ሁሉ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሚያስተምረው እና ቤተክርስቲያን በዘመናት እንዴት እየመራ እንዳለ ማወቅ አለብን፡፡ ከዚያም እኛ ከቅዱሳት መጻሕፍት ሥር ሆነን ሕይወታችንን፣ አስተሳሰባችንን ለማስተካከል ፈቃደኞች እንሆናለን፣ ምክንያቱም እኛ የእግዚአብሔር አብ፣ የወልድ እና የመንፈስ እምነት ተከታዮች ነን - አዲስ ነገር የለም።*

*— ዶ/ር ኬሊ ኤም ካፒክ*

የቤተክርስቲያን ስልጣን እና ዛሬ የፕሮቴስታንት የሃይማኖት ምሁራን ከቀደሙት ባለስልጣናት ጋር የሚዛመዱበትን መንገድ ከተመለከትን ወደ ሌላ አስፈላጊ ጉዳይ መዞር አለብን። የዛሬው የሥነ-መለኮት ምሁራን የዘመኑ የፕሮቴስታንት ባለሥልጣናትን እንዴት መገምገም አለባቸው? በዘመናችን እያደጉ ያሉትን ሥነ-መለኮታዊ ቀመሮች ስልጣን እንዴት መረዳት አለብን?

## የዘመኑ ባለሥልጣናት

ቀደምት ፕሮቴስታንቶች በዘመናቸው በትክክል በተሾሙ መሪዎች የተገነባውን ሥነ-መለኮት ዋጋ አረጋግጠዋል። ነገር ግን ደግሞ በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዘመኑ ባለሥልጣናትን ከፍ ከፍ እንዳያደርጉ ተጠብቀዋል። እንደ አለመታደል ሆኖ አሁንም የዘመኑ የፕሮቴስታንት የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ብዙውን ጊዜ እነዚህን ቀደምት አመለካከቶች መከተል ይከብዳቸዋል። በራሳቸው ዘመን የሚኖሩት የፕሮቴስታንት የሥነ-መለኮት ሊቃውንት በተረዱት መንገድ ወደ ጽንፍ የመሄድ አዝማሚያ አላቸው።

በአንድ በኩል አንዳንድ የሥነ-መለኮት ሊቃውንት ዛሬ ስለ ዶክትሪን ቀመሮች ተጠራጣሪ ይሆናሉ። በሌላ በኩል ብዙዎች በዘመናችን ስለ ዶክትሪን ቀመሮች ቀኖናዊ የመሆን አዝማሚያ አላቸው። ግን የእውነተኛ ተሐድሶ ሥነ-መለኮት መንገድ ለታማኝ የአስተምህሮ ቀመሮች መጣር ነው። ስለ ወቅታዊው የአስተምህሮ ቀመሮች በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠራጠሩ የሥነ-መለኮት ምሁራን ማንኛውንም ሥልጣን ወይም ዛሬ ቤተክርስቲያን ለምትናገረው ነገር የመገዛት ፍላጎትን ሁሉ ውድቅ ያደርጋሉ። በሌላኛው ጫፍ ደግሞ እጅግ ቀኖናዊ የሆኑ የሃይማኖት ምሁራን የዘመናዊ ዘይቤዎች ፍጹም እንደሆኑ አጥብቀው ይከራከራሉ።

> ወቅታዊ የክርስትና እምነቶችን በምንገመግማቸው መንገዶች ላይ በጣም መጠንቀቅ አለብን። በአንድ በኩል በወንጌላውያን ክርስቲያኖች መካከል ብዙውን ጊዜ የሚያድግ ጥርጣሬ አለ ፣ አዲስ ነገር ስህተት ነው፤ ምክንያቱም እውነት ዱሮ ነበር የሚበል አመለካከት ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ ይህ መንፈስ ቅዱስ ዱሮ ይሠራ እንደነበር አሁንም በቤተክርስቲያን ውስጥ ንቁ እና ሕያው ሆኖ ይሠራል የሚለውን አለማመን ነው፡፡ በሌላ ጫፍ ላይ ደግሞ "ያረጀ ከሆነ፣ ካለፈው የመጣ ከሆነ፣ ለዛሬ አግባብነት የለውም። እኛ የምንፈልገው አዲስ ሀሳቦች ናቸው።" የሚል አሳብ ነው፡፡ በዚህ መንገድም መሄድ የለብንም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ዛሬ በቤተክርስቲያን ውስጥ እየሰራ ነው፤ ለብዙ ሺህ ዓመታት በቤተክርስቲያን ውስጥም ይሠራ ነበር። ስለዚህ ያለፈው እውነት እንዳለ ስንገነዘብ፣ ካለፈው በመጣው እውነት ላይ መገንባት አለብን። በሚሊኒየሙ በኩል የቤተክርስቲያን ትርጓሜዎች በዘመናችን በአስተሳሰባችን እና በኑሮአችን መንገዶች ላይ በጣም ተፅእኖ ሊኖራቸው ይገባል። አያችሁ፣ ሥነ-መለኮት በመንፈስ ቅዱስ ላይ ጥገኛ ነው፣ ቅዱሳት መጻህፍትን እንድንግር እና ቀደም ሲል ለቤተክርስቲያን የሰጠውን ጥበብ በዘመናችን ለሚያጋጥሙን ጉዳዮች ግባራዊ እንድናደርግ ይረዳናል፡፡
>
> — ዶ/ር ሪቻርድ ኤል ፕራት ፣ ጁኒየር

በዘመናችን የሚገጥመን ከባድ ጥርጣሬ እና ቀኖናዊነት በከፊል አለ ምክንያቱም የአስተምህሮ መግለጫዎች ብዙውን ጊዜ በቀላሉ እውነት ወይም ሐሰት ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ በእውነተኛ እና በሐሰት መካከል የተለያዩ አማራጮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የታማኝነት ትምህርታዊ ቀመሮችን መፍጠር የበለጠ ጠቃሚ ነው። ሁሉም ሥነ-መለኮታዊ መግለጫዎች ከማይሻረው ቅዱሳት መጻሕፍት አስተምህሮ አንጻር ሲታይ ብዙ ወይም ጥቂት እውነት ወይም ሐሰት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

በአንድ በኩል ከጥርጣሬ እይታ በተቃራኒ፣ አንዳንድ ሥነ መለኮታዊ አቋሞች የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በበቂ ሁኔታ የሚገልጹ እና እውነተኛ ብለን ልንጠራቸው እና እንደ ጠቃሚ ልንቆጥራቸው እንችላለን። አሁን እነዚህ መግለጫዎች ፍጹም አይደሉም። ግን ሌላ የሚገለጥ አንዳንድ የተሻሉ ነገሮች ካልመጡ በስተቀር እንደ እውነት ለመቀበል በቂ ናቸው።

በሌላ በኩል አንዳንድ ሥነ-መለኮታዊ አቋሞች ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት በጣም የራቁ በመሆናቸው እነርሱን እንደ ሐሰት መሰየማቸው ትክክል ነው። የዘመናዊ አስተሳሰቦችን ሥልጣን አጥብቀው ከሚይዙት በተቃራኒ አንዳንድ ነጥቦችን በኋላ ተቀባይነት እንዳላቸው እስካታመነ ድረስ እነዚህን ቀመሮች ውድቅ ማድረግ እንችላለን።

ለምሳሌ “እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ነው” የሚለውን የዘመኑ አስተምህሮ ነጥብን እንመልከት። ይህ እውነት ነው ብለን በተለምዶ ተቀብለናል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ ላይ የበላይ እንደሆነ ያስተምራል። ሆኖም ይህ መግለጫ በላዩ ላይ ሊሻሻል ስለሚችል ፣ በተወሰነ መልኩ ፍጽም አይደለም። ምናልባት ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነትን እግዚአብሔር ፍጥረትን ከፈጠረ በኋላ ከፍጥረታት ጋር ግንኙነት አያደርግም ከሚለው ትምህርት ለመለየት ከሆነ ይህ መግለጫ በእውነቱ የተሳሳተ ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል። እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ከመጀመሪያው የፍጥረት ሥራው በኋላ ከታሪካዊ ክስተቶች ጋር አይገናኝም የሚል እይታ አለ። ስለዚህ “እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ላይ ሉዓላዊ ነው” የሚለው አባባል በእርግጥ ከመለኮታዊ አቅርቦት እውነታ - እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ጋር በቅርበት እየተሳተፈ ስለሆነ - ሊያርቀን ይችላል

በመጨረሻ ከዘመናዊ ሥነ-መለኮታዊ አሰራሮች አንፃር አንዳንድ ሥነ-መለኮታዊ መግለጫዎች እንደ እውነት ለመቁጠር ለቅዱሳት መጻሕፍት በቂ ናቸው፤ ሌሎች ከቅዱሳት መጻሕፍተ ሩቅ በመሆናቸው እንደ ሐሰት ለመቁጠር ቀላል ነው፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች ቀኖናዊ መሆን እና ሁሉም ዘመናዊ አሰራሮች እውነት ናቸው ብለን መገመት ለእኛ አይጠቅመንም። ነገር ግን ተጠራጣሪ መሆን እና የዘመኑ የቤተ ክህነት ሥልጣን ዋጋን ችላ ማለት እንዲሁ አይጠቅምም። ሁሉም ሥነ-መለኮታዊ አሰራሮች ሊሻሻሉ ይችላሉ፣ ግን በእኛ ዘመን የተቀረጹ በመሆናቸው ብቻ ችላ ማለት የለብንም። ይህ ከቀድሞው ተሐድሶ ከፍተኛው - “ሁል ጊዜ ተሃድሶ” ብቻ አይደለም።

የዘመኑ የፕሮቴስታንት ሥነ-መለኮት ዓላማ የታማኝ ሥነ-መለኮታዊ አሳቦችን ማምረት ነው፡፡ እኛ እግዚአብሔር የሰጠንን ሀብቶች ሁሉ በትሕትና እና በኃላፊነት ተጠቅመን - የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ፣ በማህበረሰብ ውስጥ መስተጋብር እና ክርስቲያናዊ አኗኗር - የታመነ የአስተምህሮ ቀመሮችን እናዘጋጃለን፡፡ በተቻለ መጠን የእኛን ትምህርቶች ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርቶች ጋር ለማጣጣም እንፈልጋለን። አስተምህሮቶቻችን ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ይበልጥ በቀረቡ መጠን የበለጠ ሥልጣን ይኖራቸዋል። እነርሱ ከቅዱሳት መጻሕፍት የበለጠ ሲሆኑ ያን ያህል ሥልጣን የላቸውም። ነገር ግን በሁሉም ሁኔታዎች የቤተክርስቲያን ሥነ-መለኮት ሁል ጊዜ ለቅዱሳን መጻሕፍት በመገዛት መያዝ አለበት።




እኛ ታማኝ አስተምህሮን ማሳደግ እንድንችል እግዚአብሔር ሦስት ዋና ሀብቶችን ይሰጠናል፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት ውስጥ በሥነ-መለኮት ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እና በቤተ-ክርስቲያን ሥልጣን መካከል ያለውን ግንኙነት ዳስሰናል። በመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክ እምነት ዘመን ውስጥ ያደጉትን በርካታ አመለካከቶችን ተመልክተናል። እንዲሁም የጥንት ፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ እነዚህን አመለካከቶች እንዴት እንዳስተካከለ ተመልክተናል። በመጨረሻም የተሃድሶ አመለካከቶችን በዘመናዊ ፕሮቴስታንታዊነት ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቤተክርስቲያናዊ ስልጣን ላይ የመተግበርን አስፈላጊነት መርምረናል።

የክርስትና ሥነ-መለኮት መገንባት ሁላችንም ከሥልጣን- የቅዱሳት መጻሕፍት ሥልጣንም ሆነ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን - ጋር መታገልን ይጠይቃል። በዚህ ትምህርት ውስጥ እንዳየነው የቅዱሳት መጻሕፍትን ፍፁም፣ የማይጠረጠር ሥልጣን በጠንካራ አቋም ካላረጋገጥን ከእውነት እንስታለን፡፡ ይህ የእኛ ጥበቃ፣ በሥነ-መለኮት ውስጥ አስተማማኝ መልህቃችን ነው። በተመሳሳይ ጊዜ እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ ያደረገውን ፈጽሞ ችላ ማለት የለብንም። ከእኛ በፊት የሄዱ ፍፁም አልነበሩም። ዛሬ የቤተክርስቲያን መምህራን ፍጹም አይደሉም። ሆኖም ምንም ያህል የተሳሳቱ ቢሆኑም፣ እግዚአብሔር ልናከብርላቸው የሚገባን በቤተክርስቲያን ውስጥ ባለሥልጣናትን አስቀምጧል፡፡ እነዚህን መርሆዎች በአእምሯችን ከያዝን፣ ባለፈው እና በእኛ ዘመን የክርስትናን ሥነ-መለኮት ያጋጠሙ ብዙ ችግሮችን ማስወገድ እንችላለን። የክርስቶስን አካል የሚያገለግል እና ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣ ሥነ-መለኮት መገንባት እንችላለን።

# አስተዋፅዖ አድራጊዎች

**Vincent Bacote, Ph.D. (Host)** is Associate Professor of Theology and Director of the Center for Applied Christian Ethics at Wheaton College. Dr. Bacote holds an M.Div. from Trinity Evangelical Divinity School with an emphasis on Urban Ministry, and an M.Phil. and Ph.D. in Theological and Religious Studies from Drew University. He is a member of the American Academy of Religion, the Christian Theological Research Fellowship and the Evangelical Theological Society. A prolific writer and speaker, Dr. Bacote has authored and edited numerous books, including *The Spirit in Public Theology: Appropriating the Legacy of Abraham Kuyper* (Baker Academic, 2005) and *The Political Disciple: A Theology of Public Life* (Zondervan, 2015). He is also a regular columnist for *Comment* and has contributed to magazines such as *Books and Culture*, *Christianity Today*, and *Think Christian*. He and his family reside in the Chicago area.

---

**Dr. Biao Chen** is Director of Chinese Projects at Thirdmill.

**Dr. Steve Curtis** is Director of Timothy Two Project International.

**Dr. Jeff Dryden** is Professor of Biblical Studies at Covenant College.

**Rev. Michael J. Glodo** is Associate Professor of Biblical Studies at Reformed Theological Seminary in Orlando, Florida.

**Dr. J. Scott Horrell** is Professor of Theological Studies at Dallas Theological Seminary.

**Dr. Kelly M. Kapic** is Professor of Theological Studies at Covenant College.

**Dr. Michael J. Kruger** is President and Professor of New Testament at Reformed Theological Seminary in Charlotte, N.C.

**Dr. Dan Lacich** is a pastor at Northland, A Church Distributed in Orlando, FL.

**Dr. Jonathan T. Pennington** is Associate Professor of New Testament Interpretation and the Director of Research Doctoral Studies at The Southern Baptist Theological Seminary.

**Nicholas Perrin, Ph.D.** is the Franklin S. Dyrness Professor of Biblical Studies at Wheaton College & Graduate School.

**Dr. Gregory R. Perry** is Vice President for Strategic Projects at Thirdmill and former Associate Professor of New Testament and the Director of City Ministry Initiative at Covenant Theological Seminary.

**Dr. Richard L. Pratt, Jr.** is Co-Founder and President of Thirdmill.

**Dr. Tim Sansbury** is Assistant Professor of Philosophy and Theology and Vice President of Administration at Knox Theological Seminary.

**Rev. George Shamblin** serves at Birmingham Theological Seminary and The Center for Executive Leadership.

**Dr. James D. Smith III** is Associate Professor of Church History at Bethel Seminary, San Diego, and Adjunct Professor of Religion at the University of San Diego.

**Dr. Carey Vinzant** is Assistant Professor of Systematic Theology at Wesley Biblical Seminary.

## የቃላት ፍቺ

**ተምሳሌታዊ ትርጉም** - ሰዎችን ፣ ቦታዎችን ፣ ነገሮችን እና ክስተቶችን ለመንፈሳዊ እውነቶች ምልክቶች ወይም ዘይቤዎች አድርገው የሚይዙትን ቅዱሳት መጻሕፍት ለመተርጎም የሚተገበር አቀራረብ

**አናንግካል ትርጉም** – ጽሑፉ ስለ መጨረሻዎቹ ቀናት በሚናገረው ላይ የሚያተኩር ቅዱሳት መጻሕፍትን ክፍሎች ለመተርጎም የሚተገበር አቀራረብ

**አርስቶቴሊያን** - በጥንታዊው የግሪክ ፈላስፋ አርስቶትል ሥራዎች ላይ የተመሠረተ የፍልስፍና ወግ; በዋናነት ተግባራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ

አትናቴዎስ- (እ.ኤ.አ. በ 296-373 ዓ.ም.) ሥላሴን ያረጋገጠ እና አርዮሳዊነትን ውድቅ ያደረገ የአራተኛው ክፍለ ዘመን የእስክንድርያ ጳጳስ እና የሥነ-መለኮት ምሁር

**አውግስቲን-** (እ.ኤ.አ. በ 354-430 ዓ.ም) ቅዱሳን መጻሕፍት አስተምህሮን በተመለከተ የመጨረሻ ሥልጣን ያላቸው መሆኑን ያመነ እና የቤተክርስቲያን የሃይማኖት መግለጫዎች የቅዱሳን መጻሕፍት ትምህርት ጠቃሚ ማጠቃለያዎች አድርገው የወሰዱት የሂፖ ጳጳስ ፤ ዛሬ በቤተክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ በርካታ ሥራዎችን ጽፈዋል

**መጽሐፍ ቅዱሳዊነት** - እያንዳንዱን ሥነ -መለኮታዊ ጉዳይ ያለፈው የፕሮቴስታንት ወግ ሳይረዳ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ መወሰን እንዳለበት የሚያራምድ እይታ

**ጆን ካልቪን-** (1509-1564) የክርስትና ሃይማኖት መዋቅር የፃፈው ፈረንሳዊው የሃይማኖት ምሁር እና ቁልፍ የፕሮቴስታንት ተሃድሶ አራማጅ የነበረ

**ካሲያን ፣ ጆን-** (እ.ኤ.አ. በ 360-435 ዓ.ም.) ኳድሪጋ በመባል የሚታወቀውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አቀራረብን ያወጁ የመካከለኛው ዘመን መነኩሴ እና የሥነ-መለኮት ምሁር

**የእርግጠኛነት ሾል** - ከላይ ዋና ዋና እምነቶችን የሚወክልበት እና የታችኛው የውስጠኛውን የእምነት ደረጃን የሚያመለክት፣ በመካከላቸው ያለው ደግሞ የተለያዩ የእምነት ደረጃዎችን የሚያመለክት ሞዴል ነው::

**የኬልቄዶን ጉባኤ** - በ 451 ዓ.ም በኬልቄዶን ከተማ ውስጥ ኢየሱስ እውነተኛ አምላክ እና እውነተኛ ሰው መሆኑን ያረጋገጠ የቤተክርስቲያን ጉባኤ ነው::

**የኒቂያ ጉባኤ** - የሥላሴን አስተምህሮ ያረጋገጠ እና አርዮሳዊነትን ውድቅ ያደረገ በ 325 ዓ.ም በኒቂያ ከተማ የተደረገው የቤተክርስቲያን ጉባኤ ነው።

**ዲኮንስትራክሽን**– በጽሑፍ እና ትርጉም መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ፈላስፋ ዣክ ደርሪዳ ያዘጋጀው የድህረ-ዘመናዊ የስነ-ፅሁፍ ትንተና ጽንሰ-ሀሳብ ነው

**ዶክትሪን** - በሥነ -መለኮታዊ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ውህደት እና ማብራሪያ

**ቀኖና** - በአንድ ሃይማኖት ፣ ርዕዮተ ዓለም ወይም ድርጅት የተያዘው የተረጋገጠ እምነት ወይም ትምህርት

**አፈታት** – ከግሪክ ቃል "ትርጓሜ ወጥቷል" ወይም "ከ" የመጣ፣ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባብ ትክክለኛውን ትርጓሜ የማውጣት ሂደት

**የመጀመሪያው የቁስጥንጥንያ ጉባኤ** - በ 381 ዓ.ም የአርያን መናፍቃንን ውድቅ በማድረግ የኒቂያን የሃይማኖት መግለጫን ለመጠበቅ እና ለማስፋፋት የተካሄደ የቤተክርስቲያን ጉባኤ ነው።

**የመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ-አፈታት** - የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም እና አስፈላጊነት የመተርጎም ጥናት

**ኢግናቲየስ-** (ከ50-108 ዓ.ም. ገደማ) የቤተክርስቲያን አባት እና የአንጾኪያ ሦስተኛው ጳጳስ በርካታ አስፈላጊ ሥነ-መለኮታዊ ርዕሰ ጉዳዮችን በሚመለከት ለጥንት ክርስቲያኖች ተከታታይ ደብዳቤዎችን የጻፉ ነበር።

**መነሳሳት** - መንፈስ ቅዱስ የሰው ልጆችን የእግዚአብሔርን መገለጥ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲጽፉ እና ሥራቸውን በበላይነት በመቆጣጠር ጽሑፎቻቸው የማይሻር እንዲሆን ያደረገበትን መንገድ የሚያመለክት ሥነ-መለኮታዊ ቃል ነው::

**ኢራኒየስ-** (እ.ኤ.አ. ከ130 እስከ 202 ዓ.ም.) ግኖስቲሲስን ውድቅ በማድረግ የአራቱን ወንጌሎች ትክክለኛነት ያረጋገጠበትን ፀረ-መናፍቃን መጽሐፍን የጻፈው የሁለተኛው ክፍለ ዘመን ጳጳስ እና የጥንት ክርስቲያን ጸሐፊ።

**ጀሮም-** (ከ 345-420) የቀድሞው የቤተክርስቲያን አባት መጽሐፍ ቅዱስን ተራ ሕዝብ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ በላቲን ቩልጌት በመተርጎሙ ይታወቃል።

**የቃል በቃል ትርጉም** – የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የመጀመሪያውን ወይም ሰዋሰዋዊ-ታሪካዊ ትርጉምን የሚያመለክት ቃል ፣ የአንድ ጽሑፍ ግልፅ ወይም ተራ ትርጉም

**ሉተር ፣ ማርቲን-** (1483-1546) በ 1517 በዊተንበርግ ቤተክርስቲያን በር ላይ 95 ነጥቦችን በመለጠፍ ተሐድሶውን የጀመረው የ16 ኛው ክፍለ ዘመን የጀርመን መነኩሴ እና ፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ አራማጅ ።

**ሰማዕት ፣ ጀስቲን-**(ከ 100-165 ዓ.ም. ገደማ) ትልቅ ሰው (አዋቂ ሆኖ) ክርስትናን የተቀበለ እና በእምነቱ ምክንያት ሰማዕትነትን የተቀበለ የጥንት ክርስቲያን ተከራካሪ።

**ሜካኒካዊ አነሳሽነት -** *መንፈስ ቅዱስ በመሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስን ያዘዘ መሆኑን የሚያረጋግጥ የመነሳሳት እይታ ፣ እና የሰው ጸሐፊዎች እርሱ የተናገረውን በግልፅ መዝግበዋል የሚል ነው*

**ኒዮ-ፕላቶኒዝም-** በፕላቶ ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ የፍልስፍና ትምህርት ቤት; በፕሎቲነስ (እ.ኤ.አ. በ 205-270 ዓ.ም.) ተጀምሯል ፤ በምስጢራዊነት ላይ ድንበር የለሽ ፣ መንፈሳዊነት ትምህርት; ሕልውና ሁሉ የሚመጣው "አንድ"፣ "ፍፁም" እንደሆነ አስተምሯል

**ኦርጋኒክ መነሳሳት -** *መንፈስ ቅዱስ የሰው ልጅ ደራሲያንን ስብዕናዎች፣ ልምዶች፣ እይታዎች እና ዓላማዎች በመቆጣጠርና በማይሳሳት ጽሑፋቸውን እንደመራቸው የሚያረጋግጥ የመነሳሳት እይታ ነው።*

**ፖሊካርፕ** - (እ.ኤ.አ. በ69 -156 ዓ.ም) የሐዋርያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር የነበረውና በክርስትና እምነቱ ሰማዕትነትን የተቀበለው የሰምርኔስ የቤተ ክርስቲያን አባትና ጳጳስ።

**ብዙነት/ polyvalence -** *በሥነ -መለኮት ውስጥ ፣ ብዙ ትርጉም ወይም እሴት ደረጃዎችን ለማመልከት የሚያገለግል ቃል*

**ድህረ ዘመናዊነት** - በምክንያታዊነት እና በዘመናዊነት ሳይንሳዊ ዘዴዎች ላይ ተጠራጣሪ እና ግላዊ ምላሽ ለመግለጽ የሚያገለግል የፍልስፍና ቃል።

**የፕሮቴስታንት ተሐድሶ-** የአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን የሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንን ለማስተካከል የሞከረ፣ ግን በመጨረሻ ተለያይቶ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያንን አቋቋመ።

**ኳድሪጋ -** *አራት የተለያዩ ትርጉሞች እንዲኖሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብን ያገናዘበ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አቀራረብ*

**ህዳሴ -** በመካከለኛው ዘመናት እና በዘመናዊው ዘመን (ከ 14 ኛው እስከ 17 ኛው ክፍለ ዘመን) መካከል በጥንት የሮማን እና የግሪክ ሥነ-ጽሑፍ ፣ ሥነ-ጥበብ እና ባህል ውስጥ አዲስ ፍላጎትን ያነቃቃ "የዳግም መወለድ" ዘመን።

**የፍቅር/ሮማንትክ ተነሳሽነት -** *መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲያን እንዲጽፉ አነሳስቷቸዋል ነገር ግን ጽሑፎቻቸውን አይተቆጣጠረም ብሎ የሚያምን የመነሳሳት እይታ ነው፡፡*

***ሴምፐር ሪፎርማንዳ*** – የላቲን ቃል ትርጉም "ሁል ጊዜ ተሃድሶ"; የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣናት ሁል ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥጥር ሥር መሆን አለባቸው የሚለውን የተሐድሶ አመለካከት ያመለክታል::

***ሴንሱስ ሊትራልስ*** – የላቲን ሐረግ ትርጉሙ "ቃል በቃል ስሜት"; የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቡን የመጀመሪያ ወይም ቃል በቃል ትርጉም ያመለክታል፡፡

***ሶላ ስክሪፕቱራ-*** የላቲን ሐረግ ትርጉም "ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ"; ቅዱሳት መጻሕፍት የሁሉም ሥነ-መለኮታዊ ጥያቄዎች የበላይ እና የመጨረሻ ዳኛ እንደሆኑ ያረጋግጣል። ከተሃድሶ መሰረታዊ መርሆዎች አንዱ ነው፡፡

**ተርቱሊያን-** (ከ155-230 ዓ.ም) የጥንት ክርስቲያን ጸሐፊ እና የቤተ ክርስቲያን አባት ከካርቴጅ ማርሴዮን በመቃወም የጻፈ እና ስለ ስላሴ ለመወያየት ያገለገለውን የላቲን የቃላት ፍቺ ያስፋፋው።

**ባህላዊነት -** *ሥነ -መለኮታዊ እምነቶችን መሠረት ያደረገው በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ከማድረግ ይልቅ ለረዥም ጊዜ በቆዩ ባህላዊ እይታዎች ላይ የሚያደርግ አቀራረብ ነው*

**ትሮፖሎጂያዊ ስሜት -** በጽሑፉ ሞራላዊ ወይም ሥነ ምግባራዊ ገጽታዎች ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም የቀረበ አቀራረብ ነው

**ዩንቫሌንስ** - ልዩነት - በሥነ -መለኮት ውስጥ አንድ ቃል አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ወይም አስፈላጊነት ብቻ ለማመልከት የሚያገለግል ቃል ነው

**ዌስትሚኒስተር የእምነት መግለጫ** - በዌስትሚኒስተር መለኮታዊ ጉባኤ የተዋቀረ እና በ1647 የታተመ ትምህርታዊ ማጠቃለያ።

**ኡልሪክ ዚዊንግሊ-** (1484-1531) የስዊስ ፕሮቴስታንት መስራች ተደርገው የሚቆጠሩት ተፅዕኖ ፈጣሪ የስዊስ ተሃድሶ አራማጅና እና ቄስ